ሰባተኛው መልአክ

ከስብሐት ገብረ እግዚአብሔር



2059

MH
bate

http://ethioliberty.wordpress.com/

ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

ሰባተኛው መልአክ

ግንቦት 2000 - አዲስ አበባ

http://ethioliberty.wordpress.com/

© የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

All rights reserved

የመጀመሪያ ዕትም - 1992

ሁለተኛ ዕትም - 2000

1. ex

አሳታሚ:- ቃልኪዳን ታደሠ

የሽፍነ ስዕል:- ታምራት ገዛኸኝ

የውስጥ ዲዛይን ገጽ ቅንብር

ማኅሌት አሳታሚ

እንዴ መግቢያ

ውድ እንገብያን

ይኔ መግቢያ ከዚህ ለምታነቡት «ሰገተኛው መልእክ» ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት ላነበባችሁት <የተኰላሸ> ወይም <የተበረዘ> እትምና በቅርብ ጊዜ <እንዴወረደ> ለምናትመው «ትኩሳት» ጭምር ያገለግላል የሁለቱም ልቦለዶች መቼት ያው በመሆኑ፣ ይዘታቸው ይለያያል'ንጂ

የሰው ልጅ በመንግስት ይረጃ ተደራጅቶ መኖር ከጀመረባቸው ዘመናት መዲህ እና ቋንቋን በፅሁፍ አስፍሮ ለመጠቀ ችሙ ልዶች ማስተላለፍ ከቻለ መዲህ፣ የትም እገር ይሁን፣ በመቼም ዘመን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ይሁን፣ የሚከተለው ተደጋጋሚ ድራማ
ይከሰታል::

ስልጣንን ሶስት የተደራጁ ሀይላት
ይጋፉታል:: ሰፊው ህዝብ እንደሆነ
ዝንታለሙን በስንትና ሰንት ታታሪነት
<ጥሮ ግሮ> ይኖራል:: እንደራሊየበት
ደሞ እነዚህን ሀይላት ወደ ደሞ ጠላም
እንደየፍላጎታቸው ያገለግላቸዋል፣
ያቀማጥላቸዋል፣ ይሞትላቸዋል
[እነሱ ተኳላዎቹ እርስ በርስ
እየተዋወቁ፣ በጉ ህዝብ ግን ሳያውቅ-
ገቸው እየተቀራመቱት]

ሀ) መንፈሳዊ [ሀይማኖታዊ ወይም
ርእየተ አለማዊ] ስልጣን በዚህ
በእውነታዊ ልቦለድቹን ዘመን
እና በዋናው ገፀገህሪያቹን እገር

ከቤተ ክህነት ይሰርፃል

ለ) ወታደራዊ ስልጣን በጦር ሀይላት
አዛዥቹ ስልጣን ይተኳሳል

ሐ) ኢኮኖሚያዊ ስልጣን ኩንግድና
ትርፍ ሚስጥራዊ ትስስር፣ እና
ገንዘብ ከሚገለው ሰው ሰራሽ ተአምር
ይመነጫል

ይህ መግቢያ የሚመለከታቸው
የሁለቱ ልቦለድቹ ገፀገህሪያት ፍስታ
ተማሪዎቹ ስለሆኑ፣ እና ሁለቱም
Marxist በመሆናቸው፣ በማርክስ
እተያይ ገንዘብ ምን እንደሆነ እነሆ:-

እንበል እንድ የመቶ ብር note
ይዤ ልውጣ:: ወረቀትነው በኳሚጸ-
ትሬ እይን ብናየው:: በማህበረ ሰብ
እይን ስናውቀውና ስንሰራበት ግን
ሌላ ነው

http://ethioliberty.wordpress.com/

ምግብ ቤት ቁርሱን በልቼ፣ ያቺን መቶ
ሰጥቼ፣ መልሱን ዘጠና ተቀብዬ ኢወጣለሁ፡
ብፈልግ ለወዳጄ ቴሌግራም፣ ደብዳቤ ኢል-
ካለሁ — ወይ ስልክ ኢደውላለሁ፡ መልሱን
ሰማንያ ከምናምን ተቀብዬ ወጥቼ፣
በኦቶቡስ ወይ በታክሲ መርካቶ ሄጄ
... ኢስክ መጨረሻዋ ሳንቲም ኢቺ
መቶ ብሬ ስንት magic ኢንደምት ሰራ-
ልኝ ይታያችሁ፡ ኢዚያ ሄዳ ደም ሌሎች
ሰዎች ሌሎች ተኢምራት...
ኢስክዚህ ድረስ <ትኩ ሳት> ኢና
<ሰገተኛው መልኢክ> ተመሳሳይ ናቸው፡
በኢንድ መፀሀፍ በተጠቃለሉ ነበር፡ ግን
መሰረታዊ የሆነ ልደነት ኢላቸው
ኢንዳቸውን የሚመራቸው የፍቅር
መንፈስ... ውጤቱ ኢዎንታዊና
ኢስደሳች

ሌላቸውን የሚነዳቸው የጥላቻ
መንፈስ... ውጤቱ ኢሉታዊና
ኢሳዛኝ
ከኢንዲ መልካም ደስታ
ከሌላው መልካም ሀዘን
ኢመኝላቸ ጓለሁ
ስብሐት ለኢብ

http://ethioliberty.wordpress.com/

አንድ

ፈረንሳይ አገር በምማርበት ጊዜ፡-

አንድ አመት ያህል ከአየለ ነብር ጋር አሳልፌአለሁ። ንዴቱ በቶሎ ስለሚንፍል እዚያ ዩኒቨርሲቲ የምንማር ሀበሾች ነብር እንለው ነበር

ያን ጊዜ አየለ ነብር ከእኔና ከያሲን በቀር ሰው ነያስጠጋም ነበር። ለምሳሌ አንድ ቀን ብቻውን ዉሴንትራ» የተባለው ካፌ (ቡና ቤት) ውስጥ ቁጭ ብሉ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሲጃራ እያጨሰ ቢራ ሲጠጣ አንድ አሜሪካዊ ተማሪ መጥቶ በፈረንሣይኛ

«እዚህ መቀመጥ እችላለሁ?» አለው

አየለ በእንግሊዝኛ «ይኸ ነፃ አገር ነው። የፈለግህበት ልትቀመጥ ትችላለህ» አለው

«እንግሊዝኛ ትናገራለህ?» አለው አሜሪካኑ

«አዎን»

«ጥሩ ነው»

«ምኑ ነው ጥሩ?» አለ አየለ

«እኔ ፈረንሳይኛ ስለሚያዳግተኝ በእንግሊዘኛ ልንወያይ እንችላለን»

አየለ «ኮሙኒስት ነህ?» አለው

«ኧረ በጭራሽ!» አለ አሜሪካኑ

«እንግዲያው እኔና አንተ እንዴት ልንወያይ እንችላለን? እንኳን መወያየት አብረን ልንቀመጥ አንችልም»

«ለምን?» አለ አሜሪካኑ

«እኔ ክኢምፔሪያሊስት ካፒታሊስት ጋር ልቀመጥ ከብሬ አይፈቅድማ!» አለውና ቢራውን ይዞ ተነስቶ ወደ ሌላ ባዶ ጠረጴዛ ሄደ

አየለ ይህን ሲነግረኝ «ለምን እንዲህ አደረግህ?» አልኩት

«ያንኪሶችን ማበሳጨት በጣም ደስ ይለኛል» አለኝ

«ለምን?» ስለው

«እነሱ የሚሰሩትን ጉድ፣ በሰው ልጆች ላይ የሚፈፅሙት ግፍ መቼ አጣኸው?» አለኝ

አሜሪካኖቹ በመካከለኛውና በደቡብ አፍሪካ ላይ፣ በሩቅና በቅርብ ምስራቅ እና በየሀገሩ የውስጥ ጉዳይ እየገቡ የሚፈተፍቱትን «ቀፋፊ ነገር» አንድ በአንድ ያውቃል። በራሳቸው ሀገር ውስጥ ጥቁሮቹን፣ ቀይ ህንዶቹን ምን ያህል እንደሚጨቁኑአቸው . . . አበጥሮ ያውቃል። ስለ አሜሪካኖቹ ወሬ በተነሳ ቁጥር ይበሽቃል። «እውነት መነገር አለበት» ይልና፣ የአሜሪካኖችን ቀፋፊ «አሰቃቂ» ተግባር አንድ በአንድ ይዘረዝራል

ግን የሚጠላው የአሜሪካኖቹን ብቻ አይደለም

አንድ ማታ (አሁንም ለምሳሌ ያህል) እንደ ልማዱ ካፌ ሌንትራ ውስጥ ቁጭ ብሎ ቢራ እየጠጣ ሲጋራ ሲያጨስ አንዱ ፈረንሣይ ሰውዬ መጣና አጠገቡ ከተቀመጠ በኋላ፡-

«የየት አገር ሰው ነዎት?» አለው

አየለ «የቢሾፍቱ» አለው

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ቢሾፍቱ? የት ነው እሱ?››

«ቢሾፍቱ ውስጥ ነው»

«እሱማ ነው። ማለቱ አስያ ውስጥ ነው፣ አፍሪካ ውስጥ ነው፣ ወይስ የትኛው ክፍለአለም ውስጥ ነው?» አለ ፈረንሣዩ

«አላውቅም»

«የትኛው ክፍለአለም ውስጥ እንኳ እንደሆነ አያውቁም?»

«አላውቅም»

«ትንሽ ጂኦግራፊ አልተማሩም?»

«አላውቅም»

«አዚህ ዩኒቨርስቲ ተመዝግበዋል?»

«አላውቅም»

«ምን የሚያውቁት ነገር አለ»

«ምንም»

«ከፈረንሣዮች ጋር መነጋገር አይፈቅዱም?»

«አልፈቅድም»

«ካገሬው ጋር ለመወያየትና ሣጣብ ለመለዋወጥ ካልሆነ አዚህ ሀገር ምን ሊያደርጉ መጡ?»

«ምንም»

«ይቅርታ አድርገልኝ። ብቻዎን ላይዎት እንግድነት የተሰማዎት መስሎኝ ላጫውትዎት መጣሁ እንጂ ላስቸግርዎት አልመጣሁም»

አየለ ዝም አለው። ፈረንሣዩ ተነስቶ ሄደ። አየለ ይህን ሲያጫውተኝ አሁንም

«ለምን እንዲህ አደረግህ?» አልኩት

«ነጭ አልወድም» አለኝ

«ለምን?›

«አልወዳቸውማ! እኛን ጥቁሮችን ያጠቁናል፣ ያጫውቱብናል። ሀብታችንን የሚገፉት እንዳይበቃቸው ክብራችንንም ጭምር ይገፋሉ። የሰው ልጅ መብታችንን ይረግጠብናል»

ከ1492 ዓ.ም (በፈረንጅ አቆጣጠር) ጀምሮ ባለፉት አምስት መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ ነጮች በጥቁሮች ላይ የሰሩትን ግፍ፣ ያፈረሷቸውን የአፍሪካ መንግሥታት፣ እንደ ግል እርሻቸው የተከፋፈሏቸውን የአፍሪካ ሀገሮች፣ እንደ ከብት እየነዱ ባሪያ ያደረጓቸውን አፍሪካዊያን፣ አሁን በጊዜአችን አሜሪካና ደቡብ አፍሪካ ውስጥ በጥቁሮች ወገኖቻችን ላይ የሚፈፅሙትን ጭቆና፣ ነጮች በጥቁሮች ላይ የሰሩትንና አሁንም የሚሰሩትን አስቃቂ ግፍ አንድ በአንድ ያውቃል። ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቀው ሁሉ በመሉ ቢባዥ አምስት ስድስት መፅሐፍ የሚበቃው አያመስለኝም። ነጮች በኛ በኑኑቮች ላይ የሰሩትን አረመኔያዊ ጭካኔ በሰፊው ያወራል። በተለይ

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሚያዘወትራት አንዲት ታሪክ አለች:: እሷን በተናገረ ቁጥር ይስቃል:: የንዴት ሳቅ::የቁጭት!

አውሮፖ ውስጥ ያለችውን ቤልጅግ አፍሪካ ውስጥ ያለችው ኮንጎ በሰፋት ሰባሰባት ጊዜ ትበልጣታለች:: በመጀመሪያ እቺ ሰፊ ለምለም ኮንጎ የዳግማዊ ሊዎፖልድ የግል ርስቱ ነበረች:: የቤልጅግ ቅኝ ሀገር ሳትሆን የንጉሡ የግል ሀብቱ:: ታዲያ በ—— አመተ ምህረት (አመተ ምህረቱን አየለ ደጋግሞ ነግሮኝ ነበር፣ ግን ረሣሁት) ቤልጅጎች ሲያዩ ጊዜ ወንዶች ኮንጎዎች በዝተዋል:: በጣም በዝተዋል:: የሚያሰጋ ብዛት ነው:: እንዴ! እነዚህ ጥቁር ቂሎች ድንገት ተነስተው የንጉስ ሊዎፖልድ የግል ገንዘብ አይደለንም ያሉ እንደሆነስ? እወነት ነው፣ እግዚአብሔር ኮንጎን ለምለምና በማዕድን እጅግ ሀብታም አድርጎ የፈጠራት ለክርስቲያን አገልጋዩ ለንጉሥ ሊዎፖልድ ሲል ነው:: ግን እነዚህ አረመኔ ጥቁሮች የእግዚአብሔር ቅዱስ እቅድ የት ይገባቸዋል? ወንጌልንስ የት ያውቃሉ? እነሱ የሚያውቁት ከበሮ እየመቱ እስክስታ እየወረዱ መባዛት መባዛት መባዛት! እህ! እግዚአብሔር ብዙ ተባዙ መሬትንም ሙሏት ያለው እነሱን መሰላቸው እንዴ?! አበዙት እኮ ይሄን መባዛት

ቤልጅጎች፣ ስለዚህ አስፈሪ ጉዳይ ምን ይሻላል? አሉ:: ዙሪያቸውን ተመለከቱ፣ ታሪክንም አነበቡ

«አውስትራሊያ ውስጥ ነጮቹ ተወላጆቹን በምን ዜዴ ነው ሀገራቸውን የነጠቁአቸው? በመፍጀት ነው:: አሜሪካ ውስጥ ነጮቹ አዝቴኮቹን፣ ኢንካዎቹን፣ ማያዎቹን እና በብዙ የሚቆጠሩትን የቀይ ህንድ ነገዶች እንደ አፓቼ፣ እንደ ኢረኮይ፣ እንደ ኮማንቼ፣ እንደ አራፖሆ ያሉትን ታላላቅ ነገዶች፣ እነዚህን ሁሉ ህዝቦች ነጮች እንዴት አድርገው ነው ስልጣኔያቸውን ያጠፉባቸውና ሀገራቸውን የነጠቁአቸው? በመግደል:: ጦር ወይም ቀስት የሚያነጣጥርብህን በግ ህዝብ በጠመንጃ መፍጀት ምን ያቅታል? ፈጅተሃቸው ስታበቃ፣ ከነሱ የነጠቅክውን ሀገር «sweet land of Liberty» ትላለህ:: አለቀ በቃ»

እዚህ ላይ አየለ ስለአውስትራሊያና ስለአሜሪካ ልዩ ልዩ የጭካኔ ታሪክ በሰፊው ይዘረዝርና

«በኮንጎ የተደረገው ግን ኮሚክ ነገር ነበር» ይላል:: «ባለስልጣኖቹ ወታደሮቻቸውን ሰበሰቡና ብዙ ጥይት ሰጥተው ሲያበቁ «ጥቁሮቹን ወንዶች ግደሉ» ብለው አዞቧቸው:: ግን ለጠላት ፕሮፓጋንዳ እንዳይመች፣ ማለት ቤልጅግ የቅኝ ሀገሯን ህዝብ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ትፈጃለች እንዳይባል፣ ወታደሮቹ እንደ ጦር ሰራዊት ሳይሆን እንደ ግል ሰዎች ለብቻ ወይም ለሁለት ሶስት እየሆኑ እየዞሩ እንዲገድሉ ተወሰነ:: «እንደ አደን ቁጠሩት» ተባሉ:: ታዲያ ወታደሮቹ ጥይት ተቀብለው ይሄዱና፣ ጥቁሮቹን ወንዶች በማደን ፋንታ ጫካ ገብተው አውሬ ሲያድኑ ውለው ማታ ካምፕ ይመለሳሉ:: ስንት ገደልክ ሲባሉ፣ አምስት ስድስት ሰባት ይላሉ:: ይኼ አምስት ስድስት ሰባት በወታደሮቹ ቁጥር ተባዝቶ እንደገና በቀኖቹና በሶምንቶቹ ሲባዛ ብዙ ብዙ ሺ ይመጣል:: ግን ባለስልጣኖቹ ሲመለከቱ ጥቁሮቹ ወንዶች በጭራሽ አልተቀነሱም!

ባለስልጣኖቹ ገባቸው:: አዲስ ትዕዛዝ አስተላለፉ:: ይኸውም እያንዳንዱ ወታደር በተሰጠው ጥይት ጥቁር ወንድ መግደል አለበት:: ለመግደሉም ማስረጃ ይሆን ዘንድ ማታ ሲመለስ ለያንዳንዷ የተተኮሰች ጥይት የጥቁር ወንድ እጅ ከራሳው ቆርጦ አምጥቶ ለአለቆቹ ማስረከብ አለበት:: እንደ ደረሰኝ አይነት ነገር መሆኑ ነው::

ወታደሮቹ ትዕዛዙን ተቀበሉ:: ግን አምስት ስድስት ሰባት ጥቁር ከመግደል፣ ጫካ ገብቶ አውሬ ሲያድኑ መዋል ይበልጥ ደስ ይላል:: ስለዚህ ወታደሮቹ እንደ ቀድሞ ልማዳቸው ጫካ ይውላሉ

ሲመሽ አንድ መንደር ይገቡና ጥቁሮቹን ወንዶች ያሰልፏቸዋል:: ወታደሮቹ ሰይፋቸውን መዘው «በል እንግዲህ ጐበዝ» ይባባሉና የጥቁሮቹን ወንዶች እጅ ቆርጠው፣ እንደ ማገዶ እንጨት ተሸክመው፣ እንደ ድንች በጆንያ ቋጥረው ወደ ካምፕ ይመለሳሉ:: ለባለስልጣኖቹ ያስረክባሉ:: ባለስልጣኖቹ ይህን ደረሰኛ ቸውን ተቀብለው ሲያበቁ በነጋታው ሌላ ጥይት ይሰጧቸዋል:: ወታደሮቹ አሁንም አደን ይውላሉ:: ሲመሽ ሌላ መንደር ሄደው ሌሎች እጆች ቆርጠው ቆርጠው ተሸክመው ካምፕ ይገባሉ

«አንድ ቀን ባለስልጣኖቹ ነቁ:: ተመለከቱ:: አሁንም ጥቁሮቹ ወንዶች በጭራሽ አልተቀነሱም:: ግን ይሄ «ጥቁር አደን» የሚፈፀምበት ክፍለሀገር ውስጥ አብዛኛው ጥቁር ወንድ አንድ እጁ ተቆርጧል:: ሀገሩን እጀ ቆራጣ ሞልቶታል:: ባለስልጣኖቹ ስቀው ሊሞቱ!»

አየለ ይስቃል:: ብቻ ነጫጭ ትክክል ጥርሶቹ ጠይም ፊቱ ውስጥ ሲያብለጨልጩ ይታያሉ እንጂ ሳቁስ ሳቅ አይደለም:: ንዴት ነው:: እንደተዳፈነ እሳት በየጊዜው ቦግ እያለ የሚቀጣጠል ንዴት

እንዲህ አይነቱ ጭካኔ ውስጥ ውስጡን እየበላው ስለሚውል ይመስለኛል ዩኒቨርስቲው ምግብ ቤት አራት ስንበላ ነጮቹን ተማሪዎች የሚገላም

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጣቸው። አይ መገላመጡን ሲችልበት! ነጮቹን ሲያይ ረዘም ያለ ጠይም ፊቱ ላይ የኩራት ደመና ያንዣብባል። ቆንጆ ከንፈሮቹ በንቀት ይገጠማሉ። ድልህ አይኖቹ የንዴት እሳት ለብሰው ያንን የሚያዩትን የነጭ አድፍ የሚያቃጥሉ ይመስላሉ

ይህን ቁጣውን እያየን ነበር «ነብር» የምንለው የምንማረው ኤክስ (ኤክስ - አን - ፕሮሻንስ) የምትባል በደቡብ ፈረንሣይ ማርሰይ አጠገብ የምትገኝ ትንሽ የዩኒቨርስቲ ከተማ ውስጥ ነበር

ማናችንም ብንሆን መጀመሪያ እንደመጣን ሰሞን በእንግድነት ምክንያት ፈረንሣዮቹን ሴቶች ማግኘት በጣም ያስቸግረን ነበር። ለመጀመሪያው ሁለት ሶስት ወር የሴት ገላ ብርቅ ሆኖ እየታየን፣ ግብረስጋ እየራበን እየጠማን፣ ባጠገባችን ሴት ባለፈች ቁጥር ያቁነጠንጠን ነበር። «ወይ አንተ አምላክ፣ እምስ የመስቀል ወፍ የሆነበት ጊዜ መጣ!?» እያልን እንቀልድ ነበር። ልክ በአስራ አራት በአስራ አምስት አመታችን እንደምናደርገው፣ እየተሰበሰብን ብዙ የብልግና ወሬ እናወራ ነበር። ከሩቅ፣ እንዳንዶቹም እንደሚሉት በፖስታ፣ እምስ ላክልን እያልን ለቁልቢው እንሳል ነበር። በኋላ ላይ ሀገሩን እየለመድነው ሄድን። የሴት ገላ የመስቀል ወፍ መሆኑ ቀርቶ «አዶይ አበባ»

ሆነልን። እንደልባችን እንምሰው ጀመር። ተሰብስበን የብልግና ወሬ ማውራቱን ትተን ሴቶቹ ወደመሩን እንበታተን ጀመር

አየለ ነብር ግን አመቱን መሉ ሴት አላገኘም። ምክንያቱ አስከ አሁንም ቢሆን በደምብ አልገባኝም። እርግጥ ነው፣ አየለ አጭር ነው፣ ግን ቅርፀ በጣም የተስተካከለ ሆኖ፣ በፊጣን እርምጃው ሲሄድ በጣም ያምርበታል። ደሞ በቁመትም ከሱ የሚያጥሩ ሴት አየለዋወጡ ይደሰታሉ። (ዩኒቨርስቲያችን ውስጥ ሴቶቹ ወንዶቹን በብዛት በጣም ይበልጧቸዋል።)

አየለ ሴቶች ፊት በጣም አይናፋር ነው፣ ግን የወንድ አይንአፋርነት የሚማርካቸው ብዙ ሴቶች አሉ። የአየለ መልከመልካም ጠይም ፊት ላይ ዘወትር የሚታየው የኩራት ገፅ ደግሞ ሴቶችን ይሰባል እንጂ አያስጠላም። ስለዚህ አሁን ሳስበው፣ አየለ ያን አመት ሴት ለማግኘት ያልቻለው ወይም ከልቡ ስላልፈለገ ነው፣ ወይም ደሞ ጊዜ ስላልነበረው ነው አላለሁ

መጀመሪያ ነገር ለሴቶች ጊዜ አልነበረውም። ተኝቶ አርፍዶ ተኝቶ ይውልና ከሰዓት በኋላ ወደዘጠኝ ተኩል ላይ ከአልጋው ይነሳል። እኔ ቤት ይመጣል። እዚያ እኔንና ያሲንን ስናወራ ወይም ስናነብ ያገኘናል።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ይገባና «coffee, coffee, coffee!» ይለናል:: ያሲን ተነስቶ ቡና ይጥዳል

አየለና ያሲን ስለኮሙኒዝም ማውራት ይጀምራሉ

ሁለት

በምሳና በአራት ሰዓት ያሲን ይሄድና ዩኒቨርስቲው በር አጠገብ አንዲት ዛፍ ስር ይቆማል:: የሚያውቋት ተማሪዎች ሁሉ ሰምን እዚያ እንደሚቆም ያውቃሉ! ምሳውን ወይም እራቱን የሚያበላው ሰው ፍለጋ ነው:: ጠርተው ያበሉታል:: በጣም ውብ ስለሆነና በጣም ተወዳጅ ስለሆነ ያበሉታል (ከፈረንሣይ መንግሥት እንደኛ እስኮላርሽፕ የለውም:: ከሀገሩም ገንዘብ የሚልክለት ሰው የለም)

ማታ ጥሩ ፊልም ያለ እንደሆነ ያሲን ይሄድና ሲኒማው በር ላይ ይቆማል:: የሚያውቋት ተማሪዎች

http://ethioliberty.wordpress.com/

ገንዘብ አዋጥተው ትኬት ይገዙለታል። ከፊልሙ በኋላ ተሰብስበው ካፌ ሲገቡ ከነሱ ጋር ይወሰዱትና ቢራ ያጠጡታል። ማታ የሆነ እንደሆነ እና ናይት ክለብ ወይም ፓርቲ የሄዱ እንደሆነ ከእነሱ ጋር ይወስዱታል። ከናይት ክለብ ወይም ከፓርቲው ወጥተው ወደየቤታቸው ሲበታተኑ ያሲንን አንጂ ትወስደዋለች፣ ከሷ ጋር ታሳድረዋለች (የራሱ የሆነ ማደሪያ የለውም) በነጋታው የሷ ጓደኛ የሆነች ልታሳድረው ትችላለች። በያሲን የመጣ ሴቶቹ አይቀያየሙም። ሁሉንም እኩል እንደሚወዳቸው ያውቃሉ

ያሲን የሃያ አምስት ዓመት ጐረምሳ ነው። ግን አነስተኛ ሰውነቱ፣ ጢም የሌለበት ፊቱና ንፁህ ፈገግታው የአስራ አምስት ዓመት ልጅ ያስመስለዋል። አረብ እንደመሆኑ መጠን፣ ቆዳው ነጭ ሳይሆን ቡናማ የማር ወለላ የሚመስል ቀለም ነው። ከግራ በኩል የተከፈለው ረጅም ፀጉሩ በጣም ከመጥቆሩ የተነሣ ወደ ሰማያዊነት ይቃጣዋል። ሀር ከሚመስሉ ትንድቦቹ ስር ትላልቅ ጥቋቁር አይኖቹ በረሻም ሽፋል ታጥረዋል፣ ልስልስ ያለ ብርሃን ይሰጣሉ። አፉ ጠበብ ያለ ሆኖ ከንፈሮቹ የጥንታዊ ግሪክ ሀውልት ውብ ከንፈሮች ይመስላሉ። ነጭ ትክክል ጥርሶቹ በውብ ፈገግታ

ብልጭ ይላሉ። በጠቅላላ እጅግ በጣም የተዋበ ልጅ ነው

ጠባዩም የመልኩን ያህል ውብ ነው። ስለዚህ የትም ቢሄድ ሰዎች በርህራሄ ይቀበሉታል፣ ልዩ አስተያየት ያደርጉሉታል

ለምሳሌ ፓስፖርቱ ቀኑ ካለፈ ዘመን የለውም፣ ግን የፓስፖርት ችግር ገጥሞት አያውቅም። ፈረንሣይ ሀገር ልዩ የመኖሪያ ፍቃድ ሳያወጡ ከሶስት ወር በላይ ለመኖር አይቻልም (አብዛኛው ሀገር ውስጥ እንደዚህ ይመስለኛል) ያሲን ግን ያለፍቃድ ፈረንሣይ ሀገር ውስጥ ሲኖር አምስት ዓመት አልፎታል። ልዩ የስራ ፈቃድ ያልተሰጠው ባዕድ ሰው ፈረንሣይ ሀገር ውስጥ ስራ ሲይዝ አይችልም። ያሲን ግን ሥራ በየጊዜው ይይዛል። ሁለት ሶስት ወር ይሰራና ይተወዋል። ሰርቶ ያጠራቀማት ገንዘብ ስታልቅ በገንዘብ በኩል የሚያግዘው ሰው ከሌለ እንደገና ስራ ይይዛል።

ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚያግዘው ያገኛል። ሸሚዙ ሲያረጅ አንዲ ሸሚዝ ትገዛለታለች፣ ጫማው ሲያልቅ ሌላዋ ጫማ ትገዛለታለች፣ ክረምት ገብቶ ሲበረደው ሲጀምር አንዲ ሹራቧን ትሰጠዋለች። ይቀበላል፣ ምግብ ሲሰጡት ይቀበላል፣ መኖሪያ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሲሰጡት ይቀበላል፣ ፍቅር ሲሰጡት ይቀበላል፣ ሁሉንም በውብ ፈገግታ ይቀበላል

የተከራየሁት ቤት ባለሶስት ክፍል ስለነበረና ለኔ አንድ ክፍል ይበቃኝ ስለነበረ፣ ያሲንን ድንክ አልጋ አምጥተህ አንዱን ክፍል ኑርበት አልኩት

አንድ ሀብታም ፈረንሣይ አልጋ ከነፍራሹ፣ ከነአንሶላውና ከነብርድ ልብሱ ሰጠው፣ ከኔ ጋር መኖር ጀመረ። ግን ቢበዛ ሶስት ሌሊት እኛ ቤት ቢያድር ነው። ሌላውን ጊዜ ልጃገረዶቹ እየወሰዱ ያሳድሩታል

በተለይ የምትወደው አይሪን የምትባል እንግሊዛዊት ነበረች

ረጅም ቀጭን ቅልጥማም ሆና ብዙ የደስ ደስ አላት። የምትናገረው እንግሊዘኛ ከሙዚቃ ያስመር ጣል፣ ስለምንም ነገር ደንታ የላትም፣ ያሰኛትን ነገር ነው የምትሰራው። ሌሊት ሰባት ስምንት ሰዓት ላይ ያሲን ትዝ ያላት እንደሆነ ከአልጋዋ ተነስታ ወደኛ ቤት ትመጣለች። አንዳንድ ጊዜ ደሞ ከያሲን ጋር ለማደር ትመጣና፣ ቁጭ ብላ ትንሽ ካወራች በኋላ ድንገት ብድግ ብላ ደህና እደር ብላው ትወጣለች

አንድ ሌሊት አልጋ ውስጥ ተጋድሜ ሳነብ ድንገት ከተፍ አለች። ያሲን ስለሌለ በሽቃ «Bugger!»

አለችና ጫማዋን አውልቃ ወደዚያ ወርውራ የኔን የቤት ጫማ አደረገች

«በሽቅሽ?» አልኳት

«I was just in the mood to make love» አለችኝ። ነጭ ሸሚዝና ቡኒ ሱሪ የለበሰ ረጅም ቀጭን ሰውነቷን አየሁት። ደስ ይላል። እንደዚያ ረጅም ቀጭን አየመሰለች ቂጣ ወፍራም ነው። ጉንጯ ጉድጉዶ፣ ፊቷ የተራበ ይመስላል። ግን ከንፈሮቿ ወፍራም ሆነው ጉረሱኝ ጉረሱኝ ይላሉ። እንደ መፍዘዝ ያሉ አረንጓዴ አይኖቿ ስለሰጋዊ ደስታ የምታስላስል ያስመስላታል

«ግድ ከያሲን ጋር መሆን አለበት?» አልኳት። ይህን ለማለት አስቤ ነበር? ዝም ብላ አየችኝ። ወፍራም ከንፈሮቿን ሳታላቅቅ ፊቷ ላይ የሚጫወተው ፈገግታ «ግድ ያሲን መሆን የለበትም፣ ግን ከያሲን እኩል የሚችልበት ወንድ መሆን አለበት» የሚል አይነት ነበር

ትንሽ በአይኗ ከቃኘችኝ በኋላ በጣም ባጭሩ የተቆረጠ ወርቃማ ፀጉሯ ውስጥ ጣቶቿን አስገብታ ወደኋላ አያስኬደች «ደህና አደር» አለችኝና ዘወር ብላ ትልቅ ቂጧን እየወዘወዘች ወደ ያሲን መኝታ ቤት ገባች

http://ethioliberty.wordpress.com/

ተነስቼ መግቢያ በሩን ቆለፍኩትና ተከተልኳት። እጆቿን ቀጭን ረጅም ሽንጧ ላይ እድርጋ ቆማ በፈዘዙ አይኖቿ ታየኛለች

ተጠጋኋት፣ አቀፍኳት፣ በቁመት ትበልጠኛለች። ካልተንጠራራሁ አልደርስባትም። ረጅም አንገቷን ላስ ላስ አደረኩት። እንደ ድመት በጉሮሮዋ የቁጣ ድምፅ እያሰማች ትንሽ ጉንበስ ብላ ወፍራም ከንፈሯን አጉረሰችኝ

ከዚያ በኋላ እንግዲህ፣ እንደ ልማዷ ሌሊት ትመጣና ያሲንን ያጣች እንደሆነ ከኔ ጋር ታድራለች

አንድ ሌሊት እኔና እሷ አልጋዬ ውስጥ እንቅልፍ ተኝተን ሳለን መብራት ሲበራ ነቃሁ። እሷም ነቃች። ሁለታችንም ራቁታችንን ነን። ተቃቅፈናል። ያሲን ከበላያችን ቆሟል። በጣም ደነገጥኩ፣ አፈርኩ። በሃሣቤ፣ እቺ ንፍጣም እንግሊዝ ለካ በሩን አልቆለፈችም ኖሯል ብዬ በሷ ላይ ተናደድኩ። ምንም ለማድረግ ምንም ለማለት አልቻልኩም። ዝም ብዬ ያሲንን ወደላይ ማየት ሆነ

እሱም ቃል አልተናገረም፣ ውብ ፊቱ ደም ለብሷል፣ ግን በቁጣ ይሁን፣ በእፍረት ይሁን፣ ወይስ

በሌላ ስሜት ይሁን ለመገመት አልቻልኩም። በጣም ስላፈርኩና ግራ ስለገባኝ የማስተዋል ችሎታዬ ደንዝዞ ነበር

ያሲን በዝግታ ልብሱን ማውለቅ ጀመረ። ምን ሊያደርግ ይሆን ብዬ እየተደነቅሁ ቆየሁ። በመጨረሻ ሙታንታውን አውልቆ ራቁቱን ቆሞ ወደታች ያየናል። ብልቱ ግትር ብሎ ትርትር ይላል። ገና ዛሬ ራቁቱን እየሁት። ገላው ብዙ ጡንቻ የለውም። ፀጉርም የለውም። እንደ ጉሪምሳ ገላ አያስጠላም። እኔ ጥግ እንደተጋደምኩ እሱ ከዳር በኩል አልጋችን ውስጥ ገባ። አይኔን ማመን አልቻልኩም። መብራቱን አጠገቤ ባለው ማጥፊያ አጠፋሁት

በጭለማው ውስጥ ሲሳሳሙ ሲተነፍሱ እየተሰማኝ፣ ገላዎቻቸው ሲጣበቁና ሲላቀቁ የሚያሰሙት እርጥብ ድምፅ እያስጨነቀኝ፣ የአይሪን ለስላሳ ወፍራም ሞቃት ቂጥ እየተጠጋኝ፣ እያሻሸኝ እየተጠጋኝ ስሜቱ አላስችል ሲለኝ ጊዜ፣ እሱ ከፊቷ እንዳቀፋት እኔ ከኋላዋ አቀፍኳት። በልዝብ ድምፅ ውብ እንግሊዘኛዋን ታወርደው ጀመር

ትዕግስቱ አለቀ፣ ከሱ በጉልበት ነጥቄ ወደኔ አዞርኳት!! በጭለማው እየሳቀች ዞራ ወደ ጭኗ

http://ethioliberty.wordpress.com/

እርጥብ ሙቀት ውስጥ አስገባችኝ። ተራውን አፏን እንዲልሳት አንገቷን ወደሱ አዞረችለት፣ እኔ አንድ ጡቷን ጎረስኩት

ትንሽ እንደቆየን

«ልዙርልህ?» አለችው

«አልፈልግም» አላት

«እርግጠኛ ነህ?» አለችው

«እንዲህ ይሻለኛል?» አላት

«ተው. . . ቀስ በል . . . ቀስ. . . እንደሱ!» አለችው እያቃሰተች ከው አልኩ። እኔ ከፊቷ እንደገባሁ እሱ ደግሞ ከኋላዋ ገብቷል! የነገሩ እንግዳነት ለጊዜው አሸነፈኝ። ቁላዬ ውስጧ እንዳለ ድንገት ሞተብኝ። ነገሩ ገብቷት ይሁን በአጋጣሚ ይሁን እንጃ፣ አፏን አፌ ላይ ደቀነችና በጣም ሀይለኛ የሆነ እርጥብ አሳሳም ትስመኝ ጀመር። የሞተው ቁላዬ እንደገና ነብስ ዘራ። ትንሽ ቆይቼማ ያሲን ከኋላዋ እንደከተተባት ሳስብ ጊዜ ስሜቴ እየበረታብኝ፣ እንደ እንስሳ ሀይለኛ እየሆንኩ ሄድኩ

በህይወቴ እንደዚያች ያለች ሌሊት አላልፌ አላውቅም። የብልግናን ውበት፣ የቆሻሻነትን ክብር ለመጀመሪያ ጊዜ መገንዘቤና መቀበሌ ነበር።

ጧት ስነቃ እነሱ ወደ ያሲን ክፍል ሄደዋል፣ ብቻየን ነኝ። ያለፈው ሌሊት ትዝ አለኝ። ላምነው አልቻልኩም። ግን የአልጋው ሽታ አለ፣ እንሶላውም ተጨማልቋል። አይኔን ዘጋሁ። እንቅልፍ እንደገና ወሰደኝ

ከዚያ በኋላ የያሲን፣ የአይሪንና የኔ ህይወት ሌሊት ሌሊት አንድ አልጋ ውስጥ ይገመድ ይገማመድ ይፍታታ ጀመር

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሶስት

ቀን ሲሆን አይራን ወደኛ አትመጣም፤ ቀን ሲሆን ወደኛ የሚመጣው አየለ ነብር ነው

ይመጣና «coffee, coffee, coffee,» ይለናል። ያሲን ተነስቶ ቡና ይጥዳል። አየለና ያሲን ሲጋራ እያጨሱ ቡና እየጠጡ ስለኮሙኒዝም፤ ስለካፒታሊዝም፤ ስለኢምፔሪያሊዝም ማውራት ይጀምራሉ። አንዳንድ ጊዜ አብራአቸው አወራለሁ። አብዛኛውን ጊዜ ግን ዝም ብዬ ነው የማዳምጣቸው

ያሲን ድሮ ኮሙኒስት ስለነበረ ስለኮሙኒዝም ብዙ ዕውቀት አለው። ግን አሁን ኮሙኒዝምን እንደ ዘመናዊ ሃይማኖት ነው የሚቆጥረው። እንደ ሌላው

ሃይማኖት ሁሉ፤ ኮሙኒዝምም የራሱ አማኞችም አሉት፤ ቄሶችም አሉት። ልዩነቱ የኮሙኒዝምን መንግስተ-ሰማያት በህይወታችን ነው የምንወርሳት። ወደ ምድር አወረዳት እንጂ ሃይማኖት መሆኑ አልቀረም። የሌሎች ሃይማኖቶች ወግ እንዳይቀርበት እንኳ አርስ በርሱ በአምነት መከፋፈልና መወጋገዝ ጀምሯል፤ ይላል ያሲን

አየለ ግን የጋለ፤ የተናደደ ኮሙኒስት ነው። በመጀመሪያ ነገር የአሜሪካኖቹና የምዕራብ አውሮፓው ያኖቹ ኢምፔሪያሊዝም (ወይም ቅኝ ገዢነት) ያናድደዋል። ቀጥሎ አሜሪካንና ምዕራብ አውሮፓን እየታዘዙ እየተሽቆጠቆጡ የሚኖሩት የአፍሪካ፤ የእስያና የደቡብ አሜሪካ መንግስታት ያናድዱታል። ቀጥሎ የክሩሽቾቭ ሪቪገርኒዝም እና የሶቪየት ሕብረት ከአሜሪካ ጋር ተቻችሎ መኖር ያበሳጨዋል፤ በተለይም እነ ክሩሽቾቭ የስታሊንን ሬሣ ሌኒን አጠገብ ከተቀበረበት ከክብር ቦታው (ከስመ ገናናው ቀይ አደባባይ) ቆፍረው አውጥተው ስላዋረዱት በጣም ይበሽቃል። «And now, for the pleasure of the American imperialist, fat ballerinas like Kruschev are dancing and farting over stalin's grave!» ይላል። ትልልቅ አይኖቹ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ውስጥ የቁጣ ነበልባል ይቀጣጠላል። ከዚያ እንግዲህ ስለአሜሪካኖቹ ውድቀትና ስለኮሙኒዝም ድል አድራጊነት ይተነብያል

«የአሁኑ የሶቪየት ውጊያ ዩ.ኤስ.ኤ የተባለውን የበሰበሰ ዛፍ ቆርጦ የሚጥል የመጀመሪያው የምሳር ምት ነው!» ይላል

አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ወደ ዩኒቨርስቲው ምግብ ቤት እናመራለን

እንግዲህ አየለ ትላንት ማታ እራቱን እንደበላ ሌላ እህል አልቀመሰም። ዓመቱን ሙሉ እንደዚህ ነበር። አንዳንድ ቀን ከኔና ከያሲን ጋር (አንዳንዴም ከሌሎቹ ሀበሾች ጋር) እራት ይበላል

ከእራት በኋላ ካፌ ዶርቢቴል የተባለው የተማሪዎች መሰብሰቢያ ካፌ ይሄድና ቡና እየጠጣ ስለኮሙኒዝም ወይም ስለ ጥቁሮች መጨቆንና መጠቃት ይከራከራል። ካገኘው ሰው ጋር ይከራከራል። ብቻ ነጭ አይሁን፤ በተለይም አሜሪካዊ አይሁን። ወደ ሶስት ሰዓት ላይ ሌሎቹ ተማሪዎች ወደየጥናታቸው ወይም ወደየሲኒማቸው ይሄዳሉ

እኔ ሲኒማ ከገባሁ አየለ ፡ብሮኝ ሲኒማ ይገባል፤ እኔ ወደ ጥናት ክሄድኩ እሱ ወደካፌ

«ሴንትራ» ይሄዳል። ከኔ ጋር ሲኒማ ከገባ ከሲኒማ መልስ (ወደ አኩለ ሌሊት ላይ) እኔ ወደ መኝታዬ ስሄድ እሱ ወደ ካፌ ሴንትራ ይሄዳል። ግራም ነፈስ ቀኝ፣ አየለ ሌሊቱን የሚያላልፈው ካፌ ሴንትራ ውስጥ ነው

ይሄ ካፌ ሴንትራ የሌሊት መጠጊያ ነው። እንቅልፍ አምቢ ያላቸው ጉረምሶች፣ ከባሎቻቸው የተጣሉ ሴቶች፣ ሌሊት አረፍት የነፈጋቸው ሰዎች እዚህ ካፌ ቁጭ ብለው እየጠጡ፣ የግል ሀሳባቸውን እያሰቡ፣ ወይም የጋራ ሀሳባቸውን እየተወያዩ፣ ፀሐይዋ እስክትወጣላቸው ይጠብቃሉ። አብዛኛዎቹ ግራ የገባቸው፣ ህይወት ያስደነገጣቸው፣ ኑሮ የከበዳቸው፣ እንቅልፍ የሸሻቸው የሌሊት ሰዎች ናቸው

አየለ ሁለት ፓኮ ሲጋራ ይገዛና ለብቻው አንድ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብሎ ሲጋራውን እያጨሰ፣ ጋዜጣ መፅሔት ወይም መፅሐፍ እያነበበ ሲጠጣ ያመሻል። ወደ አስራ አንድ ሰዓት ላይ የሚያነበው ነገር አልገባ ሊለው ይጀምራል፤ ስካር አንጐሉን ይሸፍነዋል። አሁን እንግዲህ እንቅልፍ ሊወስደው ይችላል። ሂሣቡን ከፍሎ ወደ ዩኒቨርስቲ ይሄዳል። (ሲራመድ ፊፅሞ አይንገዳገድም) መኝታ ቤቱን ይከፍታል፤ አልጋው

http://ethioliberty.wordpress.com/

ውስጥ ይገባል፤ እንቅልፍ ይወስደዋል። ለቁርስ አይነሳም፤ ለምሣም አይነሳም። ዘጠኝ ሰዓት ላይ ከእንቅልፉ ይነቃል፤ ወደኔ ቤት ይመጣል

«Coffee Coffee Coffee» ይላል። ያሲን ተነስቶ ቡና ይጥዳል። አንዳንድ ቀን ግን በተለመደው ሰዓት ወደኛ ቤት አይመጣም። እንቅልፍ አሸንፎታል ማለት ነው። የአራት ሰዓት ሲደርስ እኔና ያሲን ወደ መኝታ ቤቱ ስንገባ፤ ተዘግቶ ብዙ ሲጋራ የተጨሰበት ብዙ ሰዓት የተተኛበት የጠባብ ክፍል ሽታ ነው። መስኮቱን እንከፍታለን

በትልልቅ ቀያይ ፊደላት «Revolution» የሚል አርእስት የተፃፈባቸው መፅሔቶች በየቦታው ተዝረክርከዋል። አንድ አምስት ስድስቱ የጥናት ጠረጴዛው ላይ ተበታትነዋል፤ አንድ ሁለቱ ወንበሩ ላይ ተቀምጠዋል። አንድ ሶስቱ ራስጌ ኮሞዲኖው ላይ ተጋድመዋል፤ አንድ ሁለቱ ወለሉ ላይ ወድቀዋል፤ አንድ አስሩ መፅሐፍ መደርደሪያው ላይ ስፍራ ይዘዋል። ክፍሉ ውስጥ ሌሎች ጥቂት መፅሄቶችና መፅሐፎችም አሉ። ነገር ግን ወዴትም ብትመለከት ትላልቅ ቀያይ ፊደላት «Revolution» እያሉ እንደ ነበልባል እየዘለሉ ወደ አይንህ ስለሚወረወሩ፤ ክፍል

ውስጥ ከ«Revolution» በስተቀር ሌላ ነገር ያለ አይመስልህም

ታዲያ ቀስ ብለህ ስትመለከት ሌላ ነገርም አለ። የጥናት ጠረጴዛው የሲጋራ አመድ ለብሷል፤ ወለሉን የተረገጠ የተጨፈለቀ የሲጋራ ቁራጭና ግማሹ የተቃጠለ የክብሪት ስባሪ ሞልቶታል። የሲጋራ ቁራጭና የክብሪት ከሰል ሳይረግጡ ክፍሉ ውስጥ አንድ እርምጃ መራመድ አይቻልም

አልጋው ተነጥፎ የሚያውቅ አይመስልም። ዩኒቨርስቲው የቀጠራቸው አልጋ የሚያነጥፉና መኝታዎቹን የሚጠርጉ ሴቶች አሉ። ግን እነሱ በሚጠርጉበት ሰዓት አየለ በሩን ቆልፎ ተኝቷል

የዩኒቨርስቲው ምግብ ቤት በጣም ትልቅ አዳራሽ ነው። እያንዳንዱ ጠረጴዛ ስምንት ወይም አስራስድስት ሰው ያስቀምጣል። ታዲያ እያንዳንዱ ጠረጴዛ አንድ የውሃ ገንቦ፤ አንድ ትንሽ የዳቦ ቅርጫትና አንድ የጨው ብልቃጥ ብቻ ነው ያለው። ስለዚህ ጨው ውሃ ዳቦ ፈላጊ ሰው ብዙ ጊዜ ሌሎቹን ሰዎች እንዲያቀብሉት መጠየቅ ይኖርበታል። ነገሩ በጣም ቀላል ነው።

http://ethioliberty.wordpress.com/

አንድ ጥቁር አየለን ውሃና ጨው ወይም ዳቦ አቀብለኝ ያለው እንደሆነ አየለ በጨዋ ደምብ ያቀብለዋል። እሱም ሲያስፈልገው ጥቁሩን አቀብለኝ ይለዋል። አንድ ፈረንሣዊ አቀብለኝ ያለው እንደሆነ ወስዶ ፊቱ ላይ ይደቅንለትና አንድ ጊዜ ያፈጥበታል

እንግዲህ አሜሪካኖቹ ፈረንሣይኛ ሲናገሩ ከአጣጣላቸው ያስታውቃል። ታዲያ ውሃ ዳቦ ጨው አቀብለኝ ያለው አሜሪካዊ ከሆነ አየለ ልክ እንዳልሰማ ሰው ዝም ብሎ መብላቱን ይቀጥላል። አሜሪካዊው ጥያቄውን የቀጠለ እንደሆነ አየለ እኔን «ይኼ ነጭ ቂጥ ባሪያውን አጥቷል?» ይለኛል። ቁጣ ፊቱን ያለብሰዋል። አሜሪካዊው የፈለገውን እኔ አቀብለ ዋለሁ። እኔ ርቆብኝ ልሰጠው ካልቻልኩ እንደገና አየለን አባክዎን ያቀብሉኝ ይለዋል። አየለ በቁጣ የጠቆረ ፊቱን ያዞርና ንዴት የሚውለበለብባቸውን ትልልቅ አይኖቹን ይተክልበታል። ቃል አይናገርም። ብቻ በአይኖቹ እሣት ይገርፈዋል

«አየለ!» አለዋለሁ

ወደኔ ፊቱን ያዞራል

«እንግዲህ ክብርህን ጠብቅ» አለዋለሁ

«ታዲያ እኔ የማንም ነጭ አሽከር ነኝ?!» ይለኛል

«እሱ ቢሆን ያቀብልህ ነበር። አሁን ህግንነቱን ተወውና አስተዳደግህን አስታውስ። በጨዋ ደምብ የጠየቀህን በጨዋ ደምብ አቀብለው»

የተጠየቀውን እቃ እንስቶ ጠያቂው ፊት ላይ ገጭ አድርጎ ያስቀምጥለትና መብላቱን ይቀጥላል

http://ethioliberty.wordpress.com/

አራት

አንድ ቀን ያሲን «ስለ እየሰ ነገር እንዴት ይሻላል?» አለኝ

«እንዴት ማለት?» ብለው

«አንድ ቀን ራሱን እንዳይገድል ፈራሁ» አለኝ

«ለምን ራሱን ይገላል?»

«ጥላቻ በዛበታ! ይህን ሀገር ወይም ይህን ሰው እወዳለሁ ሲል ሰምተኸው ታውቃለህ? እሱ የሚያስበውና የሚናገረው ስለሚጠላቸው ሀገሮች ብቻ ነው። አሜሪካኖችን ይጠላል፣ ነጮችን ይጠላል፣ አረቦችን ይጠላል፣ ሌላ ቀርቶ ሀበሾችንም ይጠላል።

ካንተ በቀር ማንንም ሀበሻ አይጠጋም። እኔን የሚጠጋኝ ካንተ ጋር ስለሚያገኘኝና ስለኮሙኒዝም ከሱ እኩል ስለማውቅ ነው። ግን ኮሙኒዝምን አይወድም»

«እንዴት?»

«እሱ ኮሙኒዝምን የሚቀበለው አሜሪካኖቹንና ምዕራብ አውሮፓውያንን የሚያጠፋ መሣሪያ ሆኖ ስለሚታየው፣ ሀብትን ከሀብታሞች ነጥቆ ሀብታሞችን የሚያጉሳቁል መስሎ ስለሚታየው ነው እንጂ እውነተኞቹ ኮሙኒስቶች እንደሚያምኑት ኮሙኒዝም ለሰው ልጆች እውነተኛ መድኃኒት ነው ብሎ ስለሚያምን አይደለም። ይገባሃል የምልህ?»

«ይገባኛል»

«አስተውለሃል? ጥላቻ ብቻ ነው አፈቱ ገፅታ ላይ ጉልቶ የሚታየው። በጥላቻ ሀይወቱን እያቃጠለ ይኖራል። ምክንያቱም ራሱን በሀይል ስለሚጠላ ነው»

«ለምን?»

«ራሱን ይጠላል» አለ ያሲን «ለምን መሰለህ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ የሚበላው? ለምን መሰለህ ከሊጋራና ከመጠጥ ጋር ብቻ የሚኖረው? ለምን መሰለህ መኝታ ቤቱ ውስጥ ተዘግቶ ታፍኖ ቆሻሻ መሀል ተኝቶ የሚውለው? ራሱን ለመግደል ነው።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሰምን መሰለህ አጋጣሚ ባገኘ ቁጥር ለሜሪካኖቹን የሚገላምጣቸውና ነገር የሚፈልጋቸው?»

«ለምንድነው?»

«ስለሚጠላቸው ሊሰድባቸው ሊያዋርዳቸው ሊደበድባቸው ሊገድላቸው ሊያጠፋቸው ይፈልጋል። ግን ሌላ ፍላጎትም አለው»

«ምን ሌላ ፍላጉት?»

«አነሱ ደብድበው እንዲገድሉት ይፈልጋል»

«ትቃጣለህ?» አልኩት

«ዝም ብለህ አስተውለውና አለመቃጠቴን ታያለህ። ሲግሞንድ ፍሮይድን ብታነብ ስለ አየለ ብዙ ነገር ይገለፅልሃል»

«እሺ፣ እንደ አንተ ሀሳብ አየለ ለምንድነው ራሱን የሚጠላው?»

«ሀበሻ ስለሆነ ነው»

«አሁንስ ቅዠቱ እየባሰብህ ሄደ»

«በጭራሽ»

«አስረዳኝ እስቲ?»

«የናንተ የሀበሾች ኑሮ ወንድ ለወንድ መዋደድን በጣም ከመጥላቱ፣ ከመናቁ የተነሳ፣ ተራው ሀበሻ ወንድ ለወንድ መዋደድን እንደ ትልቅ

ሀጢአት፣ እንደ ዋና ውርደትና እንደ ቀፋፊ እፍረት ይቆጥረዋል።አውነቱን አይደለም?»

«ነው»

ግን በሰው ልጆች መካከል፣ በየትኛውም ዘመን በየትኛውም ህዝብ፣ አንዳንድ የተለዩ ወንዶች ይገኛሉ። ከአፈጣጠራቸው ይሁን ወይስ ከአስተዳደጋቸው ወይስ ከሁለቱ ይሁን አንጃ፣ ገላቸውና መንፈላቸው ወንድን እንጂ ሴትን አይወድም»

«እሺ»

«አየለ ከእንዲህ አይነቶቹ ሰዎች አንዱ ነው። ታዲያ እጣው ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወለደ። ስለዚህ እንዲህ አይነት ሰው በመሆኑ ራሱን ይጠላል፣ ይንቃል። ልብ አድርግ፣ ይሽ ሁሉ ለአየለ በግልፅ አይታየውም። ሀበሻ በመሆኑ እንዲህ አይነቱን ነገር ስለ ራሱ በግልፅ ለማሰብ አይችልም። ስለዚህ ይህ ሁሉ ውስጡ ሲያድግ ለራሱ አይታየውም። ገባህ?»

«የምትለው ይገባኛል፣ ግን በሀሳብህ አልስማማም። ጥላቻ በዛበት የምትለው አውነት ነው። ራሱን ስለሚጠላ እንደ ሻማ በቀስታ ሀይወቱን እያቃጠለ ይጨርሳል የምትለው አውነት ሊሆን ይችላል። ወንድ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ይወዳል ስለምትሰው ግን በጭራሽ አልስማማም። እንዲያውም ላስብበት የነበረ አንድ ነገር አለ››

«ምን?» አለ ያሲን

«አንዲት ጥሩ ልጅ አግኝቶ አንድ ወር ያህል ቢተኛትና ቢደሰትባት ይህ ጥላቻው በጣም ይቀንላል፣ ከአለም ጋር ይታረቃል። ስለዚህ አንዷን ቀስ ብለን እናያይዘው»

ያሲን ራሱን እየነቀነቀ «አንተም ራስህ ሀበሻ በመሆንህ እዚህ ውስጥ የማይታይህ ነገር አለ» አለኝ

«ምንድነው እሱ?» አልኩት

«እየለ የሚወደው አንተን ነው››

ድንግጥ አልኩኝ። ግንባሬ ላይ ላብ መጣ። ያሲን ሳቅ እያለ «አይዞህ! አንተ ወንድ ወዳጅ እይደለህም»

በኋላ ስለ ያሲን ብዙ አስብ ጀመር። ማነው ይሄ ያሲን? እሱ ሰውን ይወዳል፣ ሰውም እሱን ይወደዋል። ስለዚህ ኑሮ ወንዝ ውስጥ እንደሌሎቻችን ሳይፍጨረጨር በለሳም ይንሳፈፋል። አብረኸው ስትሆን ከንፁህ ሰው ጋር እንደሆንክ ይሰማሀል። ግን ይሄ ሰውዬ ማን ነው?

ምናልባት አይሪን ታውቀው ይሆን?

አንድ ማታ እኛ ቤት መጥታ (ያሲን አልነበረም) አልጋዬ ውስጥ ገብተን ስናወራ «ላንቺ እንደሚታይሽ ያሲን ማነው?» አልኳት

አረንጓዴ አይኖቿ የባሰውን ፈዘዙ፣ ቀጫጭን ረጃጅም ጣቶቿ መሀል ከተቀረቀረው ሲጋራ ጢስ እየኮራ እየተንቀባረረ ወደ ላይ ይመዘዛል ይጠማዘዛል። ምላሷ ብቅ ብሎ ወፍራም ቀያይ ከንፈሮቿን ልሶ ተመለሰ፣ የረጠቡ ከንፈሮቿ ላመል ከፈት ብለው፣ ትንንሽ ጥርሶቿን ያሳያሉ። መልኳ የት ላይ እንደሆነ ማየት አልቻልኩም፣ ግን እንደሷ ያሉ ውበት ያጥለቀለቃቸው ሴቶች በብዙ እንደማይገኙ አርግጠኛ ነበርኩ

ወርቅ መሣይ አጭር ፀጉሯን በአንድ እጇ ወደ ኋላ ገፋችው (ልማዷ ነው) «ያሲን ሊቅ ነው» አለችኝ «እውነተኛ ሊቅ ነው። ማለቴ፣ ዕውቀትን የሚገበየው ያንን ዕውቀት በስራ ላይ አውሎ ገንዘብ ወይም ስልጣን ወይም ዝና ለማግኘት አይደለም። ለማወቅ ብቻ ሲል ነው። ማወቅ። አለቀ በቃ። እና በጣም አዋቂ ነው»

‹‹እንዴት ማለት! በጣም አዋቂ?››

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ለምሳሌ በፍልስፍና ሊሳንስ አለው። አሁን ደሞ ይሄ አመት ሲያልቅ በሃይማኖት ጥናት ሊሳንሱን ያገኛል። አረብኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሣይኛ ያውቃል። ማወቅ ስልሀም አጠናቆ ነው። በፊት ኮሙኒስት ነበር፣ ግን ሰላማዊ በመሆኑ ከኮሙኒስቶች ጋር አልተስማማም። አጉል እምነትም የለው፣ ሃይማኖትም የለው። አሁን ምን በማድረግ ላይ እንዳለ ልንገርህ?»

«ንገሪኝ»

«አውነትን በመፈለግ ላይ ነው። እና አውነትን የት ነው የሚፈልጋት መሰለህ?»

«የት ነው የሚፈልጋት?»

«ግብረ ስጋ ውስጥ። የጥንት ሰዎች አምስንና ቁላን ያመልኩ ነበር። ለምን? የህይወት ምንጭ እምስና ቁላ ስለሆነ። የህይወት አውነቱን ለማወቅ ወደ ምንጩ እምስና ቁላ መመለስ ያስፈልጋል። እኔ ስለው ቅጥ የሌለው መዘባረቅ ይመስላል። ያሲን ሲለው ግን ውበትም አውነትም እንዳሉበት ይሰማሀል።››

‹‹ቀጥይ››

‹‹አንስሳት የሚያምሩት መቼ ነው? የስሪያ ወራት በደረሰ ጊዜ ነው። የሰው ልጆች በምን እድሜ ነው ከሁሉ ይበልጥ ውብ የሚሆኑት? በጉርምስናቸው

እድሜ ነው (በሚባዱበት ዕድሜ) ዛፎችና ሌሎች አታክልት ምናቸው ነው ውብ? አበባቸው ነው። አበባቸው ምንድነው? ለአነሱ እምስና ቁላቸው አይደለም እንዴ? ለዚህ ነው ያሲን አውነትን ግብረስጋ ውስጥ የሚፈልጋት። ልገልፅልህ የፈለግኩትን ለመግለፅ የቻልኩ አይመስለኝም፣ ብቻ. . .»

«በመጠኑ ገልፀሽልኛል። ቀጥይልኝ»

«አንድ ሴሲት አኔንና አንተን አልጋ ውስጥ አላገኘንም? ታስታውሳለህ?»

«አ...ህ»

«አኔ በሩን ስላልቆለፍኩት ነበር። አውቄ ነበር ያልቆለፍኩት»

«ለምን?»

«ያሲን ነው አትቆልፊው ያለኝ»

«አርግጠኛ ነሽ?»

«ገና አኔና አንተ መተኛት ሳንጀምር ያሲን እንደምንተኛ ያውቅ ነበር»

«እንዴት አርጎ?»

«አሱ ነዋ እንድተኛህ የጠየቀኝ»

«ለምን?»

«አርግጠኛ አይደለሁም»

«የሚመስልሽን ንገሪኝ አስቲ»

http://ethioliberty.wordpress.com/

«መጀመሪያ ለሦስት የሚደረግ ግብረስጋ በጣም ስሜት ይሰጠዋል። ስጋዊ ስሜት ማለቴ ነው። ሁለተኛ መንፈሳዊ ስሜት ይሰጠዋል»

«እንዴት?»

«ጥልቅ ህይወትን የኖረ ይመስለዋል። አየህ፣ ለሱ እንደሚታየው አንድ ብቻህን መኖር ጥልቅ አድል ነው። ሁለት ብቸኞች ተገናኝተው ለጥቂት ደቂቃዎች በግብረ ስጋ ብቸኝነታቸውን ሲያሸንፉና ሁለቱ ብቻ ሲዋሃዱ ገነት ማለት ነው። ከሁለት አልፎ ሦስት ሲሆኑ ደግሞ ከዚያም ይበልጣል፤ እዚህ አልጋ ውስጥ ለሦስት በምንተኛበት ጊዜ ለኔና ላንተ የሚታየን አንድ አይነት ግብረስጋ ብቻ ነው። ለሱ ግን ከዚያ በላይ ብዙ ሌላ ነገር፣ ብዙ ውብ ነገር ይታየዋል»

«ምን ምን ይታየዋል?»

«እኔ አላውቅም። እንደ ያሲን ቅዱስ ብሆን ምናልባት ይታየኝ ነበር»

«ያሲን ቅዱስ ነው ስትይ የሮማው ጳጳስ ይሰሙሽና!» አልኂት እየሳቅኩ

«እኔ የነሱን አይነት ቅዱስነት ክቅዱስ አልቆጥረውም» አለች ክንፈሯን በንቀት ጣል አርጋ። ‹‹እነሱ ሰውን ቅዱስ የሚሉት ምድራዊውን ህይወት

የካደ እንደሆነ ነው። እኔ ግን ሰውን ቅዱስ የምለው ምድራዊውን ህይወት በሙሉ ልብ የተቀበለ እንደሆነ ነው»

«የመንደር ቂልም ኑሮን በሙሉ ልብ ይቀበላል» አልኂት

«እርግጥ ነው። ግን የኑሮን ክፋትና አስቀያሚነት ለማየትና ለመገንዘብ ስለማይችል ነዋ። ገባህ የምልህ? ቅዱስ ማለት የመንደር ቂል ሳይሆን እንደ መንደር ቂል የሚኖር ማለት ነው። አይኑ ክፋትን እያየ፣ አንጐሉ የተንኮልንና የጮሌነትን ጥቅም እያወቀ፣ ልቡ ግን ከክፋትና ከተንኮል ንፁህ የሆነ ማለት ነው። ይሉኝታን፣ ልወደድ ባይነትን፣ ምቀኝነትን፣ ጥላቻን ከልቡ ውስጥ አስወግዶ በፍቅርና በሰላም የሚኖር ማለት ነው። ያሲን እንዲህ አይነት ሰው ነው»

«ገባኝ። ያሲን ክኔ ጋር እንድትተኚ ጠይቆሽ ነበር?»

«አዎን»

«ለምን?»

«እርግጠኛ አይደለሁም። ግን አንተን በጣም ስለሚፈልግህ ይመስለኛል››

http://ethioliberty.wordpress.com/

«እንዴት ማለት እኒን?››

«በጣም ደስ ትለዋለህ። ለኔ ደስ የምትለኝን ያህል ለሱም ደስ ትለዋለህ››

‹‹ምን ማለትሽ ነው?››

‹‹እንድታቅፈው እንድትስመው እንድትተኛው ይፈልጋል››

‹‹ምንድን ነው የምታወሪው?››

‹‹አላወቅክም ኖሯል?››

‹‹አላወቅኩም››

‹‹እውር ነህ። አይንህን ክፈት። ምን እንደሚፈልግ ልንገርህ?»

«ንገሪኝ»

‹‹እኔ ሁለታችሁ መሀል እሆን የለ? እሱም ተራውን መሀላችን ለመሆን ይፈልጋል። እሱ እኔ ውስጥ ሲገባ አንተ ደግሞ እሱ ውስጥ እንድትገባ ይፈልጋል››

‹‹ለምን?››

‹‹እንደዚህ ነዋ! እሱ ወንድም ሴትም ይወዳል። እኔ የምወደድ ዓይነት ሴት ነኝ። አንተ የምትወደድ ዓይነት ወንድ ነህ። ስለዚህ ሁለታችንንም ይፈልጋል። አስታውስ እሱ እንደኔና እንዳንተ ተራ

ሰው አይደለም። በሱ ዓይን አፍረት ወይም ፀያፍ የሚሉት ነገር የለም››

ያለችኝን ለሶስት ስናደርገው ታየኝ። አልቀፈፈኝም። በሀሳቤ የያሲንን ገላ አየሁት። ብዙ ጡንቻ የለውም፣ ፀጉር የለበትም፣ አነስ ያለ ውብ ገላ ነው። በሀሳቤ አቀፍኩት። አልቀፈፈኝም፣ ግን ከዚህ በፊት ስለ ወንድ አንዲህ ዓይነት ሀሳብ መጥቶልኝ አያውቅም

‹‹ለምን ይመስልሃል ይሄን ሁሉ የምነግርህ?››

«ለምንድነው?»

«ለያሲን ብዬ ነው»

«ትወጅዋለሽ?»

«መውደድ ብቻ አይደለም። አመልከዋለሁ። ታደርግለታለህ?››

«አልችልም» አልኳት

በሀሳቤ ግን አርግጠኛ አልነበርኩም። ዝም ብለን ቆየን። ያሲን ስለ አየለ ሲያዋየኝ አየለ ይወድሃል ብሎኝ ነበር። ምናልባት ሳይታወቀው የራሱን ስሜት አየለ ላይ ሰጥፎበት ይሆን? አይሪን ስለያሲን የነገረችኝ በገዛ ራሷ ተነሳስታ ይሆን? ወይስ ራሱ ልኳት ይሆን? ለመሆኑ እቺ አይሪን እንዴት ያለች ሴት ነች?

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ያሲን ቅዱስ ከሆነ አንቺ የሱ ደቀመዝሙር መሆንሽ ነዋ››

‹‹የሱ ደቀመዝሙር ለመሆን አልበቃም። ምክንያቱም ልቤ የተራ ሰው ልብ ነው። ከደግ ይልቅ ክፉን ይመርጣል። ነፃነቱን በይሉኝታ ገበያ ይሸጣል››

የአሁኑ አነጋገሯ የአንግሊዝ ሳይሆን የምስራቃውያን ዘዬ አለው። ከያሲን የወረሰችው አነጋገር መሆን አለበት

‹‹አንግዲያውስ ምኑ ነሽ?›› አልኳት

‹‹አንደ አገልጋዩ ልትቆጥረኝ ትችላለህ። እስካሁን ያገኘሁት ሰው ሁሉ ሲያገለግለኝ ነው የኖርኩት። ለወላጆቼ አንዲት ብቻ ስለሆንኩ እነሱ አገለገሉኝ። እንደምታውቀው ረጅም ቀጭን አስቀያሚ ቢጤ ነኝ። ግን እስክለሁን ያወቅኳቸው ወንዶች ልክ የውበት ንግስት እንደሆንኩ ያህል ተገዝተውልኛል፣ አገልግለውኛል። ብቻ ምን ልበልህ፣ በሄድኩበት እንደተገለገልኩ ነው። እና አሁን ያሲንን ማገልገል ለኔ ህይወት በቂ ለውጥ ነው።››

ሲጋራዋን በረጅሙ ሳበች፣ አይኗን ዘግታ ቆየችና ጪሱን ወደውጭ ተነፈሰች፣ ቀጠለች ‹‹ከያሲን ጋር ስሆን ሁሉ ነገር ንፁህ ነው። ከሱ ጋር ብዙ

ግንኙነት ያደረኩ እንደሆነ ምናልባት ከንጽህናው ትንሽ ያተላለፍብኝ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በብዙ ከሱ ጋር ያወራሁ እንደሆነ ከደግነቱ ትንሽ ያካፍለኛል ብዬ አምናለሁ

‹‹አየህ፣ በኛ ስልጣኔ፣ ይልቁንም በኔ ቤተሰብ አካባቢ፣ ግብረስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት፣ እንደ ሀጢያት ነው የሚታየው። ስለዚህ ያሲንን ከማወቄ በፊት ግብረ ስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት ሆኖ ባይታየኝም እንኳ እንደ ጥሩ መልካም ነገር አልቆጥረውም ነበር

‹‹ከያሲን ጋር መተኛት ከጀመርኩ በኋላ ግን ግብረስጋን በአዲስ አይን አየው ጀመር። አሁን ለኔ ግብረስጋ ንፁህ ውብ ነገር ነው። የህይወት ዳንስ ነው። በማንኛውም አይነት ብንደንሰው አወዳለሁ። አብሮኝ የሚደንሰው ወንድ ልበ ንፁህ ይሁን እንጂ በኔ ገላ የፈለገውን ቢሰራ ደስ ይለኛል። ይህ የያሲን ስጦታ ነው››

«አንቺ ራስሽም እንደ ያሲን ቅድስት ሳትሆኚ አትቀሪም›› አልኳት

አፈረች። ፊቷ ቀላ ‹‹Don't talk rot›› አለችኝና ሲጋራውን አጠፋችው። ምላሷ እንደገና ብቅ ብሎ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ቀያይ ወፍራም ከንፈሮቿን ልሶ ተመለሰ። ፊቴን ወደ ፊቷ አስጠጋሁ። የረጠቡና የተከፈቱ ከንፈሮቿን በዝግታ መላስ ጀመርኩ። ጉሮሮዋ ውስጥ የተቆጣ ድመት የሚመስል ድምጽ ይንጎራደድ ጀመር። አንድ ጡቷን እየጠባሁ የድመት ቁጣዋን እየሰማሁ ስለያሲን የነገረችኝን አስታወስኩ። በጣም ጥሩ ልጅ መሆኑ አያጠራጥርም። ቅዱስ መሆኑ ግን በጭራሽ አልታየኝም ‹‹አይ ሴቶች!›› ብዬ አሰብኩኝ ‹‹ተራ ወንድ ሲሰለቻቸው፣ ሴላውን ተራ ሰው ቅዱስ ያረጉትና በቅዱስነቱ ይደሰታሉ።›› ሳቂ አመለጠኝ

‹‹ምን ያስቅሃል?››

‹‹እኔ እንጃ›› አልኳት፣ ውሸት ከመፍጠር ይቀላል ብዬ

‹‹አብድ›› አለችኝ ጭኖቿን እየከፈተች

በሀሳቤ ወይ ቅዱስ ቁላ ወይ እብድ ቁላ መሆን አለበት›› አልኩ። ክት ብዬ መሳቅ ጀመርኩ

‹‹እብድ መሆንህን ዱሮ ነው ያወቅኩት›› አለችኝ ለመቆጣት እየሞከረች። ቀስ እያለ ሳቂ ተላለፈባት

አብረን ስንስቅ ያሲን መጣ። ልብሱን ሲያወላልቅ

‹‹የቡድንና የቡድን አባቶች››

‹‹ከቅዱስ ቁላ ከአብድ ጀላ›› የሚል ሀሳብ ላልፈቅድለት መጥቶ በሳቅ ያንከተክተኝ ጀመር። ከጭኖቿ ወጥቼ አልጋው ላይ እየተንከባለልኩ ስስቅ እነሱም ሳይወዱ አብረውኝ ሲስቁ ብዙ ጊዜ ቆየን። ያሲን ልብሱን በሙሉ አውልቆ አልጋችን ውስጥ ሲገባ የቆመ ቁላውን አይቼ በሀሳቤ «ቅዱስ ቁላ ያውና! ቅዱስ ቁላ ያውና!›› እያልኩ እንደ ትንሽ ልጅ ጮህኩ፣ እንባዬ በጉንጬ እየወረደ ሆዴን ያመኝ ጀመር። ሳቁን ለማቆም ሞከርኩ፣ አልቻልኩም። እነሱም ሳይወዱ አብረውኝ ይስቃሉ። አሁንም በሃሳቤ ‹‹ቅዱስ ቁላ!›› እያልኩ በሳቅ እየተንከተክትኩ ‹‹እብድ ቁላ የት ነህ?›› ብዬ አሰብኩ። እንሶላው ውስጥ በእጄ ቁላየን ነካሁት፣ ተኝታል። ‹‹ቅዱስ ቁላ ሲነሳ እብድ ቁላ ይተኛል? ይሄ የሚገባ ነገር ነው?» ብዬ አሰብኩ። ሳቁ ሆዴን እያመመኝ አስፈራኝ ግን ላቆመው አልቻልኩም።

አይሪን ክት ብላ እየሳቀች ‹‹እብድ አይመስልህም?›› አለችው። አየሁዋት፣ አፍንጫዋን እየሁት። «ቀይ የእንግሊዝ አፍንጫ» የሚል ሀሳብ የባሰውን አሳቀኝ። እኔ ሆዴን ይዤ ስስቅ እነሱም እየሳቁ መተቃቀፍ ጀመሩ። ከመተቃቀፉ ቡራኬ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ለመሳተፍ ስላልቻልኩ መብራቱን አጠፋሁላቸውና የእብድ ሳቄን ቀጠልኩ

አሁን ሳስበው ምንም የሚያስቅ ነገር አልነበረም

አምስት

ኤክስ ሰልችቶኝ ነበር። በፋሲካ በዓል ምክንያት የአንድ አስር ቀን እረፍት ስለነበረን፣ እና ይልቁን ሚረይ የምትባል ፈረንሳዊት እንሂድ ስላለችኝ፣ ወደ ኒስ ሄድኩና ሁለት ሳምንት አብሬአት አሳለፍኩ

ኤክስ ስመለስ (ማታ ነበር) ውሃ ጠምቶኝ ስለነበረ አንድ ካፌ ገብቼ ቢራ አዘዝኩ። አስታጥቄ መጥቶ አጠገቤ ተቀመጠ። ወፍራም ቀይ ፊቱ ላይ እንደ ማሽላ ቆሎ ከፈሰሱበት ብጉሮች አንዷን እየቆነጠጠና በህመም ፊቱን እያጨማደደ ‹‹ከመጣህ አየለን አግኝተኸዋል?›› አለኝ

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹አላገኘሁትም››

‹‹ይፈልግሃል›› ሲቆነጥጣት የነበረችው ብጉር ፈረጠች። እጁን ሱሪው ላይ ጠረግ አደረገ፣ እና ሌላ ብጉር ለመምረጥ ቂጥ መላይ ፊቱን እየዳበሰ ‹‹በጥብቅ ይፈልግሃል›› አለኝ

‹‹ለምን?›› ስለው

የያዛትን ብጉር የሚያባብል ይመስል በለስለስ ድምጽ ‹‹አብዷል። ፈረንሳይ ሃገር አሳብዶታል›› አለኝ

ሀበሾቹ ሁልጊዜ የሚሉትን ነው የደገመልኝ። ግን ድምፁ ውስጥ አንድ አይነት ደስታ የሰማሁ መሰለኝ። በሸቅሁ። ለምን ይሆን ይህን አስታጥቄን የምጠላው? ቂጡ በጣም ትልቅ ስለሆነና ጮማ ያፈነው ወፍራም ፊቱ ሳይቀር ባለአፍ ባለአይን ቂጥ ስለሚመስለኝ ይሆን?

‹‹አንተን ፈረንሳይ ሀገር አሳብዶሀል?›› አልኩት

‹‹ለምን ያሳብደኛል?›› አለኝ

‹‹ብጉራም ቂጥ ስለሆንክ ነዋ!›› ብዬ እያሰብኩ

‹‹እንግዲያው አየለን ለምን ያሳብደዋል?›› አልኩት

‹‹እኔ እንጃ›› አለኝ ‹‹ብቻ አብዷል››

‹‹አብዷል ስትል ምን ማለት ነው? እኛን ሀበሾችን ሊገባን የማይችል ብዙ የላቀ ሀሳብ ያሰባል ማለትህ ነው? እኛ ስለ እምስ ስለሹመት፣ና ምቀኝነት ስናስላስል አሱ ስለኮሙኒዝምና ስለፊቦሉሽን፣ ስለስው ልጅ መብት፣ና ስለፍትህ ያስባል ማለትህ ነው?›› አልኩት

‹‹ምን ያናድድሃል?››

‹‹አብዷል ስትል ምን ማለትህ ነው?››

‹‹አኮ ስማኝ ልንገርህ!››

‹‹እሺ አሰማለሁ››

‹‹ያለፈው ቅዳሜ ሳምንት እንደ ልማዱ ካፌ ሴንትራ ሲጠጣ አምሽቶ ጥንብዝ ብሎ ለክሮ፣ ለካ አንዱ አሳላፊ ሲጠራው ሳያየው ወይም ሳይሰማው ቀርቶ ኖሮ፣ አየለ ነብር ሆዬ ጠረጴዛውን በሀይል በጥፊ መቶ ብድግ አለና ሲያበቃ፣ ካፌ ውስጥ ላሉት ሰዎች፣ ጠርሙሶችና ብርጭቆዎች ሰፊ ዲስኩር አደረገላቸው››

አስታጥቂ የሌላውን ሰው ውርደት ወይም እፍረት ማውራት በጣም ስለሚወድ፣ አሁን እምቢ አልለማህም ብለው በግድ ተለማምጠ እንደሚነግረኝ

http://ethioliberty.wordpress.com/

አውቄአለሁ። በለዚህ አየለ ካፌ ሴንትራ ውስጥ ምን እንደተናገረና ምን እንደሰራ ለማወቅ አየፈለግኩም፣ አስታጥቂን ደስ እንዳይለው በማለት፣ ይህን ሺባ ደስታውን ሳይሰፋ እንዳያገኝ በማለት

‹‹ሰማህ አስታጥቂ›› አልኩት ‹‹በሰው መቀለድ በጣም ቀላል ነኮ ነው። ለምሳሌ አንዱ ሀበሻ ባንተ ሲቀልድ ምን አለ መሰለህ?››

‹‹ምን አለ?››

‹‹ስምን መልአክ ያወጣዋል አለ። አሁን ይህን ወንድማችንን አስታጥቂ አሉት፣ ሌላውን ሰው እንዲያስታጥቅ ማለታቸው ነው። ምክንያቱም አሱ ራሱ መታጠቅ አያስፈልገውም። ለምን በለኝ። ለምን ማለት መልካም። ወንድማችን ልጅ አስታጥቂ ባይታጠቅም ሱሪው እንዳይወልቅ ቁጡ ይከላከለዋል! አለ››

በንዴት ‹‹ማነው እንዲህ ያለው?›› አለኝ። እኔው ራሴ እንደሆንኩ ገብቶታል

‹‹አልነግርህም›› አልኩት ‹‹ነገሩን ያመጣሁት በሰው መቀለድ በጣም ቀላል መሆኑን ለመግለጽ ያህል ብቻ ነው። ስለዚህ በአየለ አትቀልድ። ፍሬ ነገሩን በጨዋ ደምብ ንገረኝ››

ሊቀጥልልኝ ሲዘጋጅ፣ ሲነግረኝ ምን ያህል እንደጓጓ በግልጽ ስለታየኝ፣ ለክፋት ብዬ ‹‹ወይም ተወው›› አልኩት ‹‹የሚነግረኝ አላጣም››

ሌላ ሰው እንዳይነግረኝ፣ ማለት እሱ መንገር እንዳይቀርበት ተንገበገበ። ቶሎ መናገር ጀመረ

‹‹እና ካፌው ውስጥ ያሉትን ሰዎች እንዲህ አላቸው ‹‹ሰማችሁ፣ እኔ የቅኝ ሀገራችሁ ተወላድ አይደለሁም፡ ኮ! ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነኝ። ኢትዮጵያዊ! ኢትዮጵያዊ›› አለና ፓስፖርቱን ከኪሱ መዘዝ አድርጎ ‹‹ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ሀበ እግዚአብሔር›› የሚሰውን ፅሁፍና ከበታቹ ያለውን አርማ አሳያቸው። በኋላ ፓስፖርቱን ኪሱ ከተተና በሱ ፋንታ የጃንሆይን ስዕል መዘዘ። እንደገና የጃንሆይን ስዕል አያዞረ ‹‹የኔ ንጉስ! ኃይለስላሴ! የኔ ንጉስ›› እያለ ለሰዎቹ ሁሉ አሳያቸው

‹‹ሰዎቹ በየቦታቸው ተቀምጠው በፀጥታ ሊያፌጡበት፣ የጃንሆይን ስዕል አንድ ጊዜ ስሞ ኪሱ ከተተና ፈረንሳዮቹን ‹‹ገና አናንተ ቆዳ ለባሽ አረመኔ ሆናችሁ በሮማ ቄሳሮች ስትገዙ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን የጥጥ ልብስ እየለበስን፣ ሀር በሚለብሱ ንጉሠ ነገስታት እየተመራን አንድ አምላክ እናመልክ ነበር።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ደሞ ራሷን የቻለች ነፃ ሀገር ሆነን ስንኖር ይኸው ሶስት ሺህ ዓመት ሆነን። አስቡበት‹ና ማን ማን እንደሆነ እወቁ!›› ብሏቸው ሲያበቃ፣ ቦዩን ‹‹Garcon!›› ብሎ ጠራው። ቦዩ ሲመጣ አየለ ከኪሱ ቦርሳውን አወጣ። ከውስጡ የመቶ ፍራንክ (ሃምሳ ብር) ወረቀት መዘዘ። ወረቀቷን ቦዩ ፊት ላይ ወረወራት። የቦዩን ፊት መታችና ወለሉ ላይ ወደቀች።

አየለ ‹‹Gardez la monnaie›› (መልሱን ለራስህ ውሰድ!) አለውና ክላፌው ወጥቶ ሄደ። መቶ ፍራንኩን ጥሎ!

‹‹ምን ይመስልሃል?›› አለኝ አስታጥቂ

‹‹ይህ ኩራትና ንዴት ነው እንጂ አብደት አይደለም›› አልኩት

‹‹ቆይ ሌላም አለ!›› አለኝ አንዲን ብጉር እየቆነጠጠ

ሌላውን መስማት አልፈለኩም። አስታጥቂን ደስ እንዳይሰው ‹‹የአሁኑ አይነት ጉዳይ ከሆነ እርሳው›› አልኩት

‹‹ሌላ አይነት ነው››

‹‹እርግጠኛ ነህ?›› አልኩት (አንዳንዴ ከፋቱ ይገርመኛል)

‹‹እርግጠኛ ነኝ›› አለኝ

ልክ መስማት እንደሰለቸኝ በመምሰል በያክመ ድምጽ ‹‹እንግዲህ እንሰማዋ እንዳመጣብን›› አልኩት

ቶሎ ቶሎ ወራውን ቀጠሰ። ገረመኝ። ቀይ ወፍራም ብጉራም ፊቱ መሀል ላይ ቆንጆ ከንፈሮቹ ዘፋት ከድን እያሉ፣ ጉራማይሌ ጥርሶቹ ብቅ ጥፍት እያሉ፣ ቀይ ምላሱ እንደነበልባል እየተንቀሰቀሰች፣ ቃላቱ ከጉሮሮው እየመነጩ ከአፉ ሲፈሱ በጣም ገረመኝ ‹‹ይኸ ፊቱ ተጎልቶ የሚንጣጣው ጉድ ምንድነው? መንጣጣት አለበት? እንደዚህ እያነለብኩት ለኔ መናገር ደስ ይለዋል? ይሄ ሰው ነው? የተሻለ አካባቢ ውስጥ አድጎ ቢሆን ኖሮ ይሄ የሰውን አፍረትና ውርደት ማውራት ይህን ያህል ስሜት ይሰጠው ነበር? የአካባቢና የአስተዳደግ አድል አግኝቶ ቢሆን ኖሮ ምናልባት ልቡ ንፁህ ሊሆን ይችል ነበር? ወይስ በተፈጥሮው ቆሻሻ ነው?››

እነዚህ ሀሳቦችና ዘመዶቻቸው ሳልፈቅድላቸው እንጎሊ ሜዳ ላይ እየጋለቡ አስታጥቂ የሚናገረውን ጆሮዬ ያዳምጥ ነበር

‹‹ክትላንት ወዲያ ከምሳ ስንወጣ፣ ምግብ ቤት ሰፈር የተገኘነውን ሀበሾች፣ ጥቁሮችና አረቦች

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሁላችንም መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ሰበሰበን። ያሲንም እዚያ ነበር››

‹‹እሺ››

‹‹እና ዲስኩር አደረገልን››

‹‹ማን? አየሰ?››

‹‹አዎን››

‹‹ምን አይነት ዲስኩር?››

‹‹ይሄ ያሲን እየዞረ ሆሞ ነው /ወንድ የሚወድ ወንድ/ ጆርናሊስት ነው/ ጋዜጠኛ/ እያለ ስሜን ያጠፋልና እባካችሁ አስታግሱልኝ›› አሰን

‹‹ያሲን ስሜን ያጠፋል አለ?››

‹‹አዎን››

‹‹ከዚያስ?››

‹‹ያሲን ይዤን ካደ››

‹‹ከዚያስ?››

‹‹ከዚያ አየሰ መጣና ያሲንን ‹‹አላደረግክ›ትም ካልክ አምንሃለሁ፣ ደስ እያለኝ አምንሃለሁ›› አለና ሳመው። ከዚያ ስብሰባው ተበተነ። ያበደ እያመስልህም?››

‹‹አያመስለኝም›› አልኩትና ተነስቼ ሂሳቤን ከፍዬ ከካፌው ልወጣ ስል፣ አሱም ሂሳቡን እየከፈለ

‹‹ወያ›ት ነው የምትሄደው?›› አለኝ

‹‹እኔ ሳላይህ ቶስ ብለህ በጥንቃቄ የተከተልከኝ እንደሆነ ወያ›ት እንደምሄድ ለማወቅ ትችላለህ›› አልኩት

በኩርፊያ ድምጽ ‹‹ለምንድን ነው የምከተ ልህ?›› አለኝ

‹‹ለጥያቄህ መልስ ለማግኘት›› አልኩትና ልሄድ ስል

‹‹ትላንትና ካዲሳባ ደብዳቤ ደረሰኝ›› አለኝ። በጣም ሊነግረኝ የፈለገው ነገር በሃሳቡ እንዳለ ያስታውቃል። መጥፎ ነገር መሆን አለበት

‹‹ጥሩ›› አልኩት

‹‹የሻረግ ታጨች›› አለ። ሆዴ ተንበራጨቀ። ጥቂት ቆይቶ ልቤ በሃይል መምታት ጀመረ። ጉልበቴ ውሃ ሆነ። የሻረግ ታጨች? ረሳችኝ በቃ? አስታጥቄና ጓደኞቹ ጉድ አደረጉኝ? አጣሉን በቃ? ውሸት መተማመንን አነቃንቆ አፈረሰው? ማን ይሆን ያጫት?

‹‹ገና ዛሬ መስማትህ ነው?›› አልኩት

‹‹ቀድመህ ሰምተህ ኖሯል?›› አለኝ አንዷን ብጉሩን እያሻሸ

‹‹አዎን›› አልኩት

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ታዲያ ምነው አልነገርከኝ?›› አለኝ

‹‹ደግሞ ውሸት ፈጥረህ እንዳታሩርሳት ብዬ ነው››

‹‹ለምን አሩርሳታለሁ?››

‹‹ከዚህ በፊት ለምን አፋረስካት? ለራስህ ፈልገሀት አምቢ ስላለችህ ነዋ! ግን አንተን አምቢ በማለቷ አትፋረድባት። አስበው አሱቲ። ቅርጽህ የተቀለበች ሴት ይመስላል። ንግግርህ ሁል ጊዜ የሴቶች የቡና ወሬ ነው። ምንህ ወንድ ሆኖ ሴቶች ሊወዱህ ይችላሉ? ኧረ ለመሆኑ ቁላ አለህ? ወይስ ሀጢአትህን በብጉሮችህ አፍ ነው የምትተፋው?››

ሲቆነጥጣት የነበረውን ብጉር ቶሎ ለቀቃት። እዚያው ትቸው ሄድኩ ‹‹ነጃሳ! ቂጥ ፈት›› እያልኩ እየተናደድኩ ወደ አየሰ ቤት አመራሁ። አራት ሰዓት ተኩል ነበር። ማታ።

ሰድስት

በሩን ሳንኳኳ በአማርኛ ‹‹ማነህ?›› አለኝ

ድምፁ የደነገጠ ይመስላል። ‹‹እኔ ነኝ ክፈት›› አልኩት

በሩን ሲከፍት የክፍሉ ሽታ መታኝ። እጁ ቀዘቀዘኝ፣ ደም ሙትቻ አጨባበጥ ሆነብኝ

‹‹ቢጣም ስፈልግህ ነበር፣ ግባ›› አለኝ። መልክ መልካም ፊቱ ላይ ይንቀባረር የነበረው ኩራት አሁን የለም። በሱ ቦታ የተዘረዘረ ከርዳዳ ጢም ይታያል።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የኩራቱን አና ቤት የወረረ ጥቁር ሙጃ ይመስላል። ገባሁ። በሩን መልሶ ዘጋው

አየሁት። ደነገጥኩ። ጉልህ አይኖቹ ውስጥ ይነድ የነበረው የቁጣ ነበልባል ወዴት በረረ? አሁን አይኖቹ ውስጥ የሚታየኝ አዲስ ነገርስ ምንድነው? ደሞስ አይኖቹ ለምን ይሸሹኖል? እንደፈራ ሰው አይን

አውነትም! አይኖቹ ውስጥ የሚታየኝ ፍርሃት ነው ለካ። የምን ፍርሃት? አየሁት። ኮሳሳ መስሉ ታየኝ። ወይስ ያለወትሮው በሽሚዝ ስላየሁት ይሆን? ደሞ ሸሚዙ እንዴት ቆሸሸል!

ፊቴን ሊያይ ይፈልጋል፣ ግን አይኖቹ ይሸሹኖል። ትንሽ አስፈራኝ። የሚያውቁት ሰው ሌላ ሰው ሲሆን ያስፈራል

አሱን እንዳላይ ከፍሉን ተመለካከትኩ። ሌላ ክፍል መሰለኝ። ግን ያው ክፍል ነው። አልጋው አልተነጠፈም። ወለሉን የተረጋገጠ የሲጋራ ቁርጥራጭና ከእላት የተረፈ የክብሪት ስባሪ አልብሶታል፣ ወለሉ ላይ ከአልጋው ራስጌ በኩል አንድ ካናቴራ ወድቋል፣ አልጋው ግርጌ የተሰቀለው ፎጣ አንድ ጫፉ ወለል ላይ ወድቋል። ያው ክፍል ነው። ታዲያ ምኑ ነው የተለወጠብኝ?

ሄዶ ጠረጴዛው ፊት ኩታ የተሰቀለበት ወንበር ላይ ቁጭ አለ። ትከሻው ጎበጥ ብሏል። ሌላውን ወምበር እያመለከተኝ ‹‹ቁጭ በላ›› አለኝ

ድምጹ የራሱ ነው! ግን አንድ ነገር ጎድሎታል። ምን? መስኩቱን ከፈትኩት። የውጭው አየር ደስ ማለቱ! ሄጀ ወምበሩ ላይ ተቀመጥኩ

‹‹መስኩቱን ከፈትከው?›› አለኝ

‹‹አዎን›› አልኩት

‹‹ለምን ከፈትከው?›› አለኝ። አይኖቹ ለአንድ አፍታ አዩኝና፣ አይኖቼ ያስደነገጡዋቸው ይመስል ብሮ ብለው ሌላ ነገር ላይ አረፉ

‹‹ይሄ ክፍል ንፁህ አየር ያስፈልገዋል›› አልኩት

‹‹ያስፈልገዋል›› አለ አንደ ገደል ማሚቶ። ከዚያ አይኖቹ አንዴ ብር ብለው አይኖቼን አየት አርገው፣ እንደገና ብር ብለው ሸሹና፣ በሚጣደፍ አነጋገር

‹‹ብጣም ስፈልግህ ነበር፣ እንኳን መጣህ· ብቻዬን ሆኜ ነበር›› አለኝ

‹‹ምነው?›› አልኩት

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ሆሞ ነው! ጆርናሊስት ነው ይሉኛል። እስቲ ምኔ ነው ሆሞ?››

‹‹ማናቸው እንዲህ የሚሉህ?››

‹‹ሁሉም ናቸው። ሁሉም›› አለና ሲጋራ አቀጣጠለ። እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ። ክብሪቱን ወለሉ ላይ ጣለው

‹‹ይሄ መስኮት ቢዘጋ አይሻልም?››

‹‹ለምን››

‹‹ደሞ መስኮት ከፋች እንዳይሉኝ ብዬ ነዋ››

‹‹አይዞህ አይሉህም። ለመሆኑ ይሄ ነገር እንዴት ተጀመረ?››

‹‹አረፍቱ እንደተጀመረ ከአፍሪካውያን ወንድሞቼ ጋር ኒስ፣ ካን፣ ሞንቴ ካርሎ ሽርሽር ሄደን ተመለስን። ስንመለስ የያሲንን ወዳጅ አገኘኋት››

‹‹አይሪንን?››

‹‹አዎን። እና ደስ አለችኝ። Let us go to my chamber አልኳት››

‹‹ለምን?›› አለችኝ

‹‹To play, to make a little love›› አልኳት። አልችልም አለችኝ። ተይው አልኳትና ሄድኩኝ። አየህ?

እና በነጋታው ሆሞ ነው፣ ጆርናሊስት ነው ይሉኝ ጀመር››

‹‹እነማን?››

‹‹እነሱ››

‹‹ለምን?››

‹‹እኔ እንጃ ምን እንዳደረካቸው። እስቲ ምን በደልካቸውና እንዲህ ይሉኛል? እስቲ ምኔ ነው ሆሞ? ምኔ ነው ጆርናሊስት? አንተና ያሲን ታውቁኛላችሁ። መጀመሪያ ያሲን የነገራቸው መስሎኝ ነበር»

‹‹ለምን?››

‹‹ስሜን ለማጥፋት››

‹‹ለምን ስምህን ያጠፋል?››

‹‹አይሪንን Let us go to my chamber ስላልካት ተቀይሞኝ መስሎኝ ነበር። ግን በኋላ ስጠይቀው ጊዜ፣ እኔ በሞራሽ እንዲህ አላልኩም፣ እንዲያውም አይሪንን Let us go to my chamber እንዳልካት አላወኩም ነበር፣ አሁን ገና ካንተ አፍ መስማቴ ነው፣ አለኝ። በጣም ጥሩ ልጅ ነውኮ ያሲን፣ አይደለም?››

‹‹ነው። እሺ ቀጥል››

‹‹እና ሆሞ ነው፣ ጆርናሊስት ነው እያሉ ሲያስቸግሩኝ ጊዜ፣ አፍሪካውያንና አረቦች ወንድሞቼን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሰበሰብኩና እንዳይደበድቡኝ፣ እንዲተውኝ አስታግሱልኝ አልኳቸው››

‹‹ማንን ነው የሚያስታግሱልህ?››

‹‹የሚሰድቡኝን ሰዎች››

‹‹ማናቸው የሚሰድቡህ?››

‹‹ሁሉም በሄድኩበት ይሰድቡኛል››

‹‹አይተሃቸዋል?››

‹‹አላየኋቸውም። ሁል ጊዜ እየተደበቁ ነው የሚሰድቡኝ››

‹‹እሺ። አስታግሱልኝ ካልካቸው በኋላስ?››

‹‹እነዚያ ስድባቸውን ቀጠሉ። ይህን ስምንት ቀን ከክፍሉ አልወጣሁም። ለእራት እንኳን አልሄድም። ብስኩት፣ ሻይ ቡና ነው የምበላው። ሃያ ፓኮ ሲጋራና ሶስት ፓኮ ብስኩት ገዝቼ እዚችው ተዘግቼ ነው የምውለው የማድረው››

‹‹ምን ትሰራለህ?››

‹‹አንድ ጥናት ይገርለሁ››

‹‹የምን ጥናት?››

‹‹ስለ ሃይማኖት›› አለኝና የሚያነባቸውን መፅሐፍት አሳየኝ

‹‹ይኼኛው የአይሁድ ሃይማኖትና የክርስቲያን ሃይማኖት እንዴት እንደሚገናኙ ይናገራል፣ ይሄ የታወቁትን ሃይማኖቶች በሙሉ ያነጻጽራል። ይሄኛው. . . ››

ሰባት መፅሐፎች፣ ሰባቱም ስለ ሃይማኖት። ስለርእስታቸውና ከማውጫቸው እንዳየሁት፣ አንዱም ስለኮሙኒዝም አይናገርም፣ አንዱም ስለሬቮሉሽን አይጠቅስም። ሬቮሉሽን! ክፍሉ ለምን እንደተለወጠብኝ አሁን ገና ገባኝ። ውስጡ ተዝረክርከው በቀይ ቀለማት ‹‹REVOLUTION›› የሚል ነበልባል ሰው አይን ላይ ይወረውሩ የነበሩት መጽሄቶች አሁን የሉም። አንዷም የለችም። ሰባቱንም መፅሐፎች ካሳየኝና ስለነሱ ከነገረኝ በኋላ

‹‹አሁን አንድ መጽሐፍ ብቻ ነው ያጣሁት›› አለኝ

‹‹ምን መፅሐፍ?››

‹‹መፅሀፍ ቅዱስ››

‹‹እኔ አለኝ። ላምጣልህ?››

‹‹አምጣልኝ››

‹‹እሺ ነገ ጥዋት ይዤልህ እመጣለሁ። እስከ አሁን ከጥናትህ ምን አገኘህ?›› አልኩት

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ይሄኛው እንደሚለው፣ ማምለክ በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ባህሪይ ነው። እንደ መብላት፣ እንደ ማሰብ፣ እንደ ግብረ ስጋ ነው። ታዲያ ምንም ሳልበድላቸው ሆሞ ጆርናሊስት ይሉኛል። ምኔ ነው ሆሞ? ምኔ ነው ጆርናሊስት? አንተና ያሲን ታውቁኛላችሁ። ከናንተ ጋር ነው የምውለው። እራቴንም የምበላው ከናንተ ጋር ነው። ታዲያ ምኔ ነው ሆሞ? ለምን እንዲህ ይሉኛል?››

‹‹ማናቸው እንዲህ የሚሉህ?››

‹‹እነሱ። ኮሪዶር ሆነው፣ ከበሩ ጎላ ተሰብስበው ‹‹ሆሞ፣ ጆርናሊስት፣ እያሉ ያወራሉ፣ ይንሾካሾካሉ፣ ይጮሃሉ። ተኝቼ ሳለሁ ‹‹ራሲስት›› ይሉኛል። እስቲ እኔ መቼ ዘር አለያለሁ? ሰዎች ሁሉም ወንድሞቼ ናቸው። እነሱ ግን ሆሞ፣ ጆርናሊስት፣ ራሲስት ይሉኛል››

የሚናገረውን ብክደው ምናልባት ይሻል ይሆናል በማለት ‹‹አይሉህም›› አልኩት

‹‹ይሉኛል። እኔ ብቻየን፣ የሚያግዝልኝ የለ። ከእናቱ ተለይቼ ሰው ሀገር መጥቼ፣ ብቻየን አግኝተው ያጠቁኛል።››

‹‹አያዘህ! ከአንግዲህ እኔ አለሁ። ልክ ልካቸውን እነግራቸዋለሁ። ከዚያ ዝም ይላሉ››

‹‹እምቢ. ቢሉህስ?››

‹‹አያሉኝም››

‹‹ቢሉህስ?››

‹‹ኤምባሲያችን ስልክ እንደውልና ልክ እናስገባቸዋለን አያዘህ››

‹‹ምን አደረጓቸው? ጢሜን ስላሳደኩ ተቀይመውኝ ይሆን? ልላጨው?››

‹‹ላሰኘህ ተላጨው››

‹‹ደስ ይላቸው ይሆን?››

‹‹እነሱ ግድ የላቸውም። ላንተ እንደተመቸህ አድርግ››

‹‹ልላጨው?››

‹‹ተላጨው››

‹‹በቃ ልላጨው?››

‹‹በቃ ተላጨው››

‹‹በምላጭ ልላጨው?››

‹‹ተላጨው››

‹‹ከዚያ በኋላ ይተውኛል?››

‹‹ይተውሃል››

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹አንተ ታግዝልኛለህ?››

‹‹ጓደኛህ አይደለሁም?››

‹‹እንግዲህ ካንተ ጋር ሲያዩኝ አይደፍሩኝም?››

‹‹አይደፍሩህም››

‹‹ኧረ እንኳን መጣህልኝ! እንኳን ደረስክልኝ! አምላክ ነው የታረቀኝ።››

ወደ ላይ እያየና እጆቹን ወደ ላይ እያርገበገበ ‹‹አምላክ ነው የታረቀኝ! እንኳን ደረስክልኝ! አምላክ ነው የታረቀኝ!›› እያለ ተነስቶ፣ ሰቤተክርስቲያን የሚሰግድ ይመስል ጎንበስ ብሎ ተንበርክኮ እግሬ አጠገብ ያለውን ቆሻሻ ወለል በአፉና በግንባሩ ይሳለም ጀመር

‹‹ተነስ፣ ተነስ›› እያልኩ ትከሻውን ይገፍ አስነሳሁት። እንባው ይወርዳል። እንባው የእፎይታ ተንፈስ ማለት ነው። እንባው እየወረደ ዒመን ተሳጨ። አልጋው ግርጌ በነበረው ቆሻሻ ፎጣ ፊቱን አደረቀ

‹‹አሁን ላጨሁት። በምላጭ ላጨሁት። እንግዲህ ምንም አይሉኝም››

‹‹ቢሉህም እኔ አለሁልህ። አይዞህ! በል ደህና እደር።››

‹‹በሩን ልቆልፈው?››

‹‹ቆልፈው››

‹‹ልቆልፈው? ክውስጥ?››

‹‹አዎን ቆልፈው?››

‹‹መስኮቱንም ልዝጋው?››

‹‹ዝጋው››

‹‹መስኮቱን ዘግቼ በሩን ልቆልፈው በቃ። ክውስጥ በቁልፍ እቆልፈዋለሁ።››

‹‹ደህና እደር››

‹‹ደህና እደር። አንተ ትሄዳለህ፣ እኔ በሩን እቆልፈዋለሁ››

‹‹ጥሩ››

‹‹ከውስጥ እቆልፈዋለሁ››

‹‹ቆልፈው። ደህና እደር››

‹‹እንኳን አንተ መጣህልኝ። እንግዲህ በሩን ቆልፈው እተኛለሁ››

‹‹ጥሩ››

‹‹መስኮቱን እዘጋዋለሁ››

‹‹ዝጋው››

‹‹ጎሽ! እንኳን አንተ መጣህ አንጂ ከእንግዲህ መስኮቱን ዘግቼ፣ በሩን ቆልፌ፣ አልጋ ውስጥ ገብቼ፣ ትራስ ተንተርሼ፣ ለጥ ማለት ነው››

http://ethioliberty.wordpress.com/

ያሲን ስለ አየለ ነብር ያለኝን አስታወስኩ። ያፈቅርሃል ነበር ያለኝ። አየለ በግጥም የተናገረ መሰለኝ። አጋጣሚ ይሆን?

‹‹ጥሩ። በል ደህና አደር›› አልኩትና ወጥቼ በሩን ዘጋሁ። በሩን ሲቆልፍ ሰማሁት። ሰፊ ጥልቅ ሀዘን ተሰማኝ። በጣም ፈራሁ። የሰው አዕምሮ ሲናወጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቴ ነበር

ሰባት

በነጋታው ረፈድ ሲል ወደ ቤቱ ሄድኩ። ሻይ አፈላሁለት። የሻይ ጀበናው ቆሽሿል፣ ስኒዎቹ እንኳን ሊታጠቡ ተለቅልቀው የሚያውቁ አይመስሉም፣ ነጭ ሽክላቸው በቆሻሻ ብዛት ግራጫ ሆኗል፣ የፊት መታጠቢያውም እንደዚሁ ንጣቱን ረስቷል

የምሳ ሰዓት ሲደርስ ወደ ምግብ ቤት አልሄድም አለ። አይዞህ እኔ አለሁ ብዬ ወሰድኩት። ስንበላ ማንንም አልገላመጠ፣ ማንንም አላየ፣ ራሱን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ወደ ሳህኑ ደፍቶ በፀጥታ በላ። ምሳችንን ልንጨርስ ስንል ድንገት ቀና ብሎ በድንጋጤ እያየኝ

‹‹አየለ አሉኝ ከወዲያ?›› አለ

‹‹የለም›› አልኩት

‹‹ስሜን ሲጠሩ ይለማኛል። ስለኔ ያወራሉ። ለምን አይተውኝም? ምን አደረኳቸው?›› አለኝ

ከምሳ በኋላ እኔ፣ ያሲን፣ አየለ እንደ ድሮአችን እኔ ቤት ቡና አፍልተን እነሱ ሲጋራ እያጨሱ ወሬ ጀመርን። ግን ስለኮሙኒዝም ወይም ስለሪቮሉሽን አንድም ቃል አልተነገረም

ትንሽ ዝም ያልን እንደሆነ አየለ ‹‹ተጫወቱ እንጂ!›› ይለናል። እናወራለን። ለጊዜው ወሬው አልቆ ትንሽ ዝም ስንል አየለ ‹‹ምነው ዝም አላችሁ? አውሩልኝ እንጂ! ለምን አታወሩልኝም?›› ይለናል። ዝምታ ያስፈራዋል

ከእራት በኋላ ቤቱ ወስጀው ስናወራ ቆይተን ‹‹በል እንግዲህ ልሂድ›› አልኩት

‹‹የት ትሄዳለህ?›› አለኝ

‹‹ላየው የምፈልገው ፊልም አለ››

‹‹እኔም ካንተ ጋር ልምጣ?››

‹‹ፊልሙ የምትጠላው አይነት ነዋ››

‹‹ግድ የለህም››

አብሮኝ ሲኒማ ገባ። ፊልሙ የጣሊያኖች ኮሚክ ፊልም ነበር። በጣም የሚያስቅ ነበር። አየለ ድሮውንም እንዲህ አይነት ፊልም አይወድም፤ እንዴ እንኳን አልሳቀም። ከሲኒማው ስንወጣ ‹‹በጣም ጥሩ ፊልም ነበር፤ አይደለም?›› አለኝ

በነጋታው ማታ እንደዚሁ ሳጫውተው አምሽቼ ‹‹በል ደህና እደር›› ስለው

‹‹ቆይ ትንሽ›› አለኝ። ቆይቼ ልሄድ ስል አሁንም ‹‹ቆይ እንጂ›› አለኝ

‹‹ፊልሙ ያመልጠኛል» አልኩት

‹‹ምናለ ከእኔ ጋር አየተጫወትክ ብታመሽ?››

‹‹ፊልሙ ዛሬ ማታ ብቻ ነው የሚታየው። እንዲያመልጠኝ አልፈልግም። የሎራንስ ኦሊቪዬ ስራ ሀምሌት ነው።››

‹‹ፊልሙ ምን ያደርግልሃል? እኔን ብታጫውተኝ አይሻልህም?››

‹‹ፊልሙ እንዲያመልጠኝ አልፈልግማ። ዛሬ ያመለጠኝ እንደሆነ ሌላ ጊዜ አላገኘውም። ፊልሙ ደሞ በጣም የተመሰገነ ነው። አንተም ታውቃለህ፤

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሼክስፒርን እንደ ሎራንስ ኦሊቪዬ አድርጎ የሚጫ ውተው የለም››

‹‹ሆም! ራሲስት! ጆርናሊስት! ኢምፔሪያሊስት! እያሉኝኮ ነው። ምናለ ከኔ ጋር ብታመሽ?››

‹‹አይሉህም። በል ደህና እደር››

‹‹ካንተ ጋር ልምጣ?››

‹‹እሺ ምን ችገረኝ››

‹‹ካንተ ጋር ልምጣ በቃ። ሰር ሎራንስ ኦሊቭዬን አብረን እናየዋለን። ጥሩ! ‹‹To be or not to be, that is the question›› ሲል አብረን እንለማዋለን፣ አይደለም?››

‹‹አዎን››

ሲኒማው ውስጥ በጨለማ ሀምሌትና የአባቱ ጣዕረ መለኮት ሲገናኙ፣ አየለ ከጎኔ ‹‹ምንድነው?›› አለኝ

‹‹ምኑ?›› አልኩት

‹‹ይሄ ነገር አስደነገጠኝ። ልቤ ፈራ›› አለኝ። እኔ ሰራሁ ከፊልሙ አንዲት ቃል እንዳታመልጠኝ ጆሮየን አሹዬ አዳምጣለሁ፣ እሱ አዚህ ይለፈልፍብኛል። ዝም አልኩት። ሀምሌትና ያባቱ

ጣዕረ መለኮት ንግግራቸውን ቀጠሉ። አየለ ‹‹አኔ ፈራሁ›› አለኝ

‹‹ታዲያ ውጣ!›› አልኩት በሹቀ

‹‹አብረኸኝ ውጣ›› አይለኝም?!

‹‹ፊልሙስ?›› አልኩት። ኮኒላችን አንዱ አሸ! አለን። እውነቱን ነው።

አየለ ‹‹ትመለሳለህ›› አለኝ ‹‹ውጭ አድርሰኸኝ ትመለሳለህ››

ዝም አልኩትና ፊልሙን ሳይ

‹‹አባክህ አስወጣኝ! ፈራሁ፣ ክፉኛ ፈራሁ!›› አለኝ

‹‹ኤድያ፣ ና እንውጣ›› አልኩት

ከጨለማው የፊልም አዳራሽ ወጣን። ቡኩት ቸራጪ አጠገብ ስናልፍ አየለ ሶኖ ብሎ እጅ ነሳትና በሚለማመጥ ድምጽ

‹‹Bon soir, madame›› አላት። ሴላ ጊዜ ቢሆን አፍንጫውን ነፍቶባት ባለፈ ነበር። ውጪ እንደደረስን ‹‹ባል ልመለስ›› አልኩት

‹‹እዚህ ትተኸኝ›› አለ ዙሪያውን በጭርሃት እየተመለከተ። የከተማው መብራት ወለል ብሎ በርጋል

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ምን እንዳትሆን ነው?!›› አልኩት። ወደ ፊልሙ ለመመለስ ችኩያለሁ።

‹‹ልቤ ፈራ›› አለ ‹‹የሚገድሉኝ ይመስለኛል፣ ሲገድሉኝ አቅደዋል። ይታወቀኛል። እኔ አሁንስ ጨነቀኝ። ጠበበኝ። ራሴን ልግደልላቸውና ልረፈው?››

‹‹የማይሆን ወሬ ለምን ታወራለህ? ምን አረካቸውና ይገሉሃል?››

‹‹እኔ እንጃ፣ እኔ እንጃ። ብቻ ሊገድሉኝ አድፍጠው እንደሚጠብቁኝ ይታየኛል። አባክህ ቤቱ አድርሰኝና ትመለሳለህ?››

‹‹ፊልሙስ?››

‹‹አድርሰኝ እኮ ትመለሳለህ። ምን ላርግ ብለህ ነው? ብቻዬን እንዳልሄድ ሆሞ! ጆርናሊስት! ራሲስት! ኢምፐሪያሊስት! እያሉ አድፍጠው ይጠብቁኛል››

እንግዲህ ፊልሙ አመለጠኝ። ወደ ቤቱ ስንሄድ አንድ ጨለም ያለ ቦታ ልንደርስ ስንል ‹‹ኧረ ጨለማው አስፈራኝ። ብርሃን ወዳለበት ቦታ ሄደን ቡና እንጠጣ?›› አለኝ

‹‹እሺ›› አልኩት››

‹‹ቡና እጋብዝሃለሁ›› አለኝ

‹‹ጥሩ››

‹‹የፈለግከውን እጋብዝሃለሁ›› ትቸው እንዳልሄድ በግብግ መደለሉ ነው። የትንሽ ልጅ ብልሃት። ካፌ ገብተን ቁጭ አልን። ቦዩ ምን ልታዘዝ ሊለኝ መጣ። አየለ ተነስቶ አጅ ነሳውና ከልዑል ወይም ከንጉስ አንድ ነገር የሚለምን ይመስል በፍርሃት አቋቋምና በከበራታ ድምጽ

‹‹አባክዎን መስዬ፣ ሁለት ሻይ ብናገኝ ደስ ይለን ነበር›› አለው

ቦዩ ግራ ገብቶት እኔን አየኝ ‹‹ሁለት ሻይ ከሎሚ ጋር›› አልኩት

ቦዩ ሊሄድ አየለ ‹‹ኧረ ባክህ አታመናጭቀው ጉድ ይፈላብናል›› አለኝ።

ቦዩ ሻዩን ሊያቀርብልን አየለ ብድግ ብሎ አጅ ሊነሳው በሽቁ በአማርኛ ‹‹ቁጭ!›› አልኩት። ቶሎ ቁጭ አለ። በጣም አሳዘነኝ

‹‹ደሞ ለፈረንሳይ ቦይ የምን አጅ መንሳት ነው?›› አልኩት

‹‹ለምን እንደሱ ትላለህ? ፈረንሳዮች ወንድሞቻችን አይደሉም እንዴ?›› ዝም አልኩት

‹‹አውራልኝ እንጂ››

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ምን ላውራልህ?››

‹የሆነ ነገር አውራልኝ:: ብቻ ዝም አትበለኝ::›› ብቻውን፣ የእብደት ምድረ በዳ ውስጥ ብቻውን፣ ሆሞ ራሲስት ጆርናሊስት እያሉ የድምጽ አውሬዎች እያጎደዱት ብቻውን፣ ከለላ ፍለጋ ይንከራተታል፣ ለመሸሸግ ይሞክራል፣ ወደ ጤነኛው አለም የሚወስደውን መንገድ ፍለጋ ይደናበራል። መንገዱ ይኖር ይሆን? የኛ ድምጽ ትንሽ ተስፋ ይሰጠዋል:: የሚሽከረከረው የእብደት ምድረ በዳ ከጤነኛው አለም ጋር በክር ተንጠልጥሏል:: ክሩ ቢበጠስ፣ ምድረበዳው እንደ እንዝርት ሽክርክር እያለ ይፈናጠራል፣ በጣም ያስፈራዋል:: የኛ ድምጽ ነው ክሩ:: ዝም ያልን እንደሆነ በደንገጠ ድምጽ ‹‹አውሩ እንጂ›› ይለናል

ከነፈ ወጥተን ወደ ምኝታ ቤቱ ሄድን:: እንደገባን

‹‹ሻይ ላፍላልህ?›› አለኝ

‹‹አሁን ጠጣሁኮ›› አልኩት

‹‹ምናለ ላፍላልህ››

‹‹የለም አልፈልግም››

‹‹ተው ላፍላልህ›› (አሁንም የትንሽ ልጅ ብልሃት)

‹‹የለም መሄድ አለብኝ››

‹‹ብቻዬን እዚህ ትተኸኝ?››

‹‹አድርለኸኝ ትመለሳለህ አላልከኝም ነበር እንዴ?›› አልኩት

‹‹ምናለ አብረኸኝ ብትቆይ ልጄ? ሆሞ፣ ጆርናሊስት ራሲስት ኢምፒሪያሊስት፣ እያሉኝ እኮ ነው››

እኔው ሻይ አፍልቼ አጠጥቼው ሳጫውተው ከቆየሁ በኋላ

‹‹በል ተኛ›› አልኩት

‹‹ትተኸኝ ልትሄድ?››

‹‹እዚህ ላድር አልችልም መቼም››

‹‹ባይሆን እንቅልፍ እስኪመጣልኝ አጫው ተኝ››

እምቢ ልለው አልቻልኩም:: እንቅልፉ ሲመጣ እንደ ትንሽ ልጅ አልጋ ውስጥ አስገብቼው፣ መብራቱን አጥፍቼለት፣ በሩን ከውጭ ቆልፌ ቁልፉን በበሩ ስር ወደ ውስጥ አሾልኬለት ሄድኩ:: ትንሽ ልጅ ሆኖ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ክር። በፍርሃት ታስሮ የቅዠት ጨለማ ውስጥ
የሚፍጨረጨር ትንሽ ልጅ

ስምንት

እኔና ያሲን ሀኪም ቤት እንውሰድህ ብንለው
አየለ በጭራሽ እምቢ አለ። ደጋግመን ለመንነው፣
ደጋግሞ እምቢ አለን። ምክንያቱን ሊነግረን
አልፈለገም።

እንግዲህ አልፎ አልፎ ሻል ይለዋል።
አንዳንዴማ ኩራትና ንዴቱ አይመለስም እንጂ ያው
የድሮው አየለ ይሆናል። ያን ጊዜ ፊቱ ላይ ክባድ
ድካም፣ አይኖቹ ውስጥ ሰፊ ሀዘን ይታያል። ብዙ
አይናገርም። መስኮቱ ፊትለፊት ወምበር ላይ ቁጭ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ብሎ ወደ ውጭ ያያል፤ ደመና የሌለበትን ንፁህ ሰማያዊ ሰማይ ባዘኑ አይኖቹ እየተመለከተ

‹‹ለው ጤንነት ካላገኘ መኖር ምን ያረግለታል?››

እኛ ለዚህ መልስ የለንም፤ ዝም እንለዋለን። እሱም ዝም ይለናል። ክፍሉ ሀዘንና ፀጥታ ይለፍፍበታል

ከጥቂት ሰዓት ወይም ከአንድ ሁለት ቀን ጤንነት‹ና ሰላም በኋላ በሽታው ያገረሽበታል፤ ባገረሸበት ቁጥር ከፊተኛው እየባሰበት ይሄዳል

የሚያስበው ሁሉ ያስፈራው ጀመር። ማንበብ ጨርሶ ተወ። የሚያጫውተው ሰው ካላገኘ ወይም እንቅልፍ ካልወሰደው፤ ዝም ብሎ ወምበር ላይ ተጎልቶ በመስኮት ወደ ውጭ ይመለከታል።

ሲነሳበትም ሲሻለውም አጠገቡ የምንገኝ እኔና ያሲን ብቻ ነበርን

ያሲን ሀበሾቹን በጣም ታዘባቸው። ሁልጊዜ አንድ ላይ ስለሚያያቸው የሚዋደዱ፤ የሚተዛዘኑ ይመስለው ነበር። አሁን ግን አንድ ላይ የሚታጎሩት ለመሰያየትና በየፊናቸው ለመሄድ ባለመድፈራቸው ብቻ መሆኑ እየገባው ሄደ። ፈተና ደርሶብናል አያሉ

አየለን ለኛ ጥሰውልን ይሄዳሉ፤ ግን ቢያንስ በቀን ሶስት ሰዓት ካፌ ውስጥ እያወሩ ወይም ካርታ እየተጫወቱ ማሳለፋቸው አልቀረም

ታዲያ እኔንና ያሲንን ሲያገኙን ስለአየለ ‹‹ምክር ለበስ ቱም ነገር›› ያካፍሉናል። ‹‹ሀኪም ቤት መሄድ አልፈልግም አለ? ወይ ጉድ! ምን ይሻላል? ምናልባት አንዳንዴ ወደ ገጠር ሽርሽር ብትወስዱት አንሳሉን ሳያድስለት ይቀራል? አልፎ አልፎ ወደ ማርሰይ ብቅ ብሎ ሴት ተኝቶ ቢመጣ ሃሳቡን ወደ ሴላ አቅጣጫ ይመራለት ይሆናል። ልጅ እንደ መክሳት ሳይል አልቀረም፤ የአላማ ስጋና ፉራፉሬ ቢበላ ነፍሱን መለስ ያደርግለት ይሆናል እኮ። መዚቃ! ለተጨነቀች ነብስ ከመዚቃ የበለጠ የሰላም መልእክተኛ ከየት ተገኝቶ! ወዘተ። ግን አየለን ለአንድ ሰዓት እንኳ ያጫወተው የለም

ብቻ አንድ ግቃ አየለን ለአራት ልወስደው ስሄድ ቤቱ ተጠርጎ ወለሉ ያብለጨልጫል። ጠረጴዛው ተወልውሏል። ወምበሮቹ ላይ፤ አልጋው ግርጌና ራስጌ፤ መስኮቱ ላይ፤ የአየለ ሸሚዞች ካናቴራዎች መታጠቢያ እግር ሹራቦች ታጥበው ተሰቅለዋል። የፊት መታጠቢያው ታጥቦ ያብለጨለ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሜል። ከመታጠቢያው በላይ ያለው መስታወት ላይቀር ተወልውሏል። ይህን ሁሉ ማነው የሰራው?

አስታጥቂ ነው። በጣም ገረመኝ።

ዘጠኝ

አንድ ቀን ለጊዜው ተሽሎት ሁለታችን ቁጭ ብለን ስናወራ ‹‹አባክህ ሀኪም ጋ እንውሰድህ›› አልኩት አይናቹ በፍርሃት እየፈጠጡ ‹‹እምቢዮ! ሀኪም አልፈልግም እምቢዮ!›› በጣም ጮኸና እየተርበተበተ ፊቱ ተንበርክኮ ጣቶቹን በፀሎት እያጣመረ ‹‹አደራህን!›› አለኝ

ሲያሳዝን! ኩሩ ሰው ተንበርክኮ እስከመለመን ሲደርስ ማሳዘኑ! ‹‹እሺ ተነስ። እንተ ካልፈቀድክ ማንም ቢሆን አይመስድህም። አይዞህ ተነስ›› እያልኩ እስኑስቼ ወምበር ላይ አስቀመጥኩት። ሻይ አፍልቼ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ከጠጣን በኋላ፣ በዝግታ ‹‹ሃኪም'ኮ ያድንሃል እንጂ አይጎዳህም›› አልኩት

‹‹የለም የለም! ሃኪም ጋ ከምሄድ ብሞት ይሻለኛል››

አንድ ነገር አስተዋልኩ ‹‹ሃኪም ጋ ከምሄድ ብሞት ይሻለኛል›› ካለ በኋላ ፍርሃቱ ድንገት ሲዘረገፍለት፣ በፍርሃት ፋንታ ፊቱ ላይ ሰላም ተዘረጋ። ከዚያ በኋላ ረጋ ባለ በጣም ሰላማዊ በሆነ ድምጽ ያናግረኝ ጀመር። ይህን ለውጥ ያን ጊዜ በደምብ አላስተዋልኩትም። ነገሩ የገባኝ በኋላ ነበር

‹‹ቀላል በሽታ'ኮ ነው የያዘህ›› አልኩት ‹‹ሰውነትህ ምግብ አንሶት፣ መጠጥና ሃላብ በዝቶበት ጤናህ ተጓድሏል። በቃ። ሃኪም እረፍት ያዝልሀል። ጥሩ ምግብ፣ ቪታሚን፣ አንቅልፍ ያዝልሀል። ባንዳፍታ ትድናለህ››

‹‹አውቃለሁ›› አለኝ ‹‹አማይገባኝ መስለህ እንዴ? ይገባኛል'ኮ። በደምብ ይገባኛል››

‹‹ምኑ ነው ሚገባህ?››

‹‹በሽታዬ ይገባኛል። እነዚያ የሚለድቡኝ፣ ሆሞ፣ ራሲስት፣ ጆርናሊስት፣ የሚሉኝ በውን እንደሌሉ፣ አእምሮዬ አራት እንደሚፈጥራቸው አውቃለሁኮ››

‹‹ይህን ታውቃለህ?››

‹‹አዎን አውቃለሁ›› አለ። ይህን ሲነግረኝ ፊቱ ላይ ሆነ ድምጹ ውስጥ ፍርሃት የለም። ምክንያቱ ያን ጊዜ አልገባኝም ነበር

ዝም ብለን ቆየን

‹‹አይገርምህም የሰው ነገር?›› አለኝ። ‹‹ከትላንት ወዲያ አስታጥቄ እዚህ መጥቶ ቤቴን ጠርጎ፣ ልብሶቼን አጥቦ ሲያበቃ ‹‹እብደት ጀምሮሃልና፣ ሳይብስብህ ጨርቅህን ሳትጥልና አገርህን ሳታስድብ፣ እኛንም ሳታሳፍር አገርህ ብትገባ ይሻላል። ምናልባት የወሲሶ ወይም የደብረ ሲባኖስ ጠበል ያድንህ ይሆናል አለኝ። እና ወጥቶ ሄደ። ይህን ብሎኝ ሲወጣ ደነገጥኩ። ሆዴ በጣም ፈራ››

(ይህን ሁሉ ሲነግረኝ በፍርሃት ሳይሆን በርጋታ ነው)

‹‹የምሆነው ጨነቀኝ። አንተን ፈለኩህ። ግን ከፍል ነበረህ። በጣም በጣም ጨነቀኝ። አንተ ወደ ምሳ ልትወስደኝ እንደምትመጣ አውቄ ነበር፣ ግን እስከዚያው ጨነቀኝ። ጠበበኝ። ሆዴ ፈራ። ተንበርክኬ ፀሎት አደረግኩ። የሰጠኸኝን መፅሀፍ ቅዱስ ከፈትኩት። ስክፍተው ‹‹ሰባተኛው መልአክም መለከቱን ነፋ›› ይላል። መለከቱ ተሰማኝ። መልአኩ መለከቱን ከነፋ በኋላ ‹‹አየለ! ሆሞ ነህ! ጆርናሊስት ነህ›› ሊለኝ ነበር፣ ግን ነቃሁበት። ገና ስሜን ሊጠራ

http://ethioliberty.wordpress.com/

አፉን ሲከፍት ቶሎ መጽሐፉን ዘጋሁት። መልእኩን ዝም ላሰኘው እነሱ ጀመሩኝ። እዚህ መተላለፊያ ከበሩ ጎላ ተሰብስበው ‹‹ሆሞ! ራሲስት! ጆርናሊስት!›› አሱኝ። አይደለሁም አይደለሁም ስላቸው፣ አሜሪካኒ ‹‹First he killed President Kennedy. Now he wants to drop a bomb on the U.S. . .›› አለቻቸው

ሌሎቹ ‹‹Yes, yes, he wants to snuff out civilization like a candle with one bomb. We must tell the CIA›› እያሱ ይዝቱብኝ ጀመር። Come, let's go tell the CIA ሲሉ፣ ልድረስባቸውና ተላስታችንኤል ልበላቸው አልኩና ቶሎ በሩን ከፈትኩት። መተላለፊያው ጭር ብሏል። ውስጡ አንዲት ሴትዮ ብቻ አለች። መተላለፊያውን ትጠርጋለች። እያለቀስኩ ከእግሯ አጠገብ ያለውን መሬት ስሜ አቤት አልኩ ‹‹ሆሞ ጆርናሊስት ራሲስት ይሉኛል›› አልኳት። እንደገና እግሯ አጠገብ ያለውን መሬት ላምኩ። ቀጥሎ እግሯን ላምኩ። ጉልበቷን ላምኩ። ጭኗን ስስም ወደዚያ ገፋችኝና እኔ ስወድቅ እሷ እየሮጠች ሄደች። ጎሽ! ሆሞ አይደለም ጆርናሊስት አይደለም ራሲስት አይደለም ተላስታችንኤል ልትላቸው መሄዷ ነው፣ አልኩና ተንፈስ አልኩ። ወደ ክፍሌ ተመለስኩ

‹‹ለሰባተኛው መልእክ ቶሎ ልንገረው፣ 'ሆሞ' አይደለሁም፣ 'ጆርናሊስት' አይደለሁም፣ ብትፈልግ

ጠራጊዎን ሴትዮ ጠይቃት። ለእነሱ ልትነግራቸው ሄዳለች›› ልበለው አልኩና መጽሀፍ ቅዱሱን ከፈትኩት። ሰባተኛውን መልእክ አጣሁት። ብፈልግ ብፈልግ፣ መጽሀፍ ቅዱሱን ባገላብጥ አጣሁት። የት ሄደ? ለምን እላው አልቆየኝም? ስለኔ ሃላቡን ለውጦ መሆን አለበት። ሆሞ፣ ጆርናሊት፣ ራሲስት እንዳልሆንኩ ገብቶት ነው። ግን ንፁህ መሆኔን ማን ነገረው? ጠራጊዎ ሴትዮ መሆን አለባት። እንዴ! እንዴ! እንዴ! ለካ ሳይገባኝ ቀርቶ ነው እንጂ ጠራጊዎ ሴትዮ የእውነት ጠራጊ አልነበረችም። ለካስ እምዬ ማርያም ኖራለች! ስጨነቅ አይታ ልትረዳኝ ወርዳ ነው። ‹‹አይ እምዬ ማርያም! ርህሩህ ልቧ አይፀና ሆዷ! ተንበርክኬ ስብሃት ለእግዝአትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ብዬ ከልቤ ምስጋና አቀረብኩላት

‹‹ስብሃት ለእግዝአትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ!›› ስል ነቃሁ። አልጋ ውስጥ ነኝ። ለካ ይሄ ሁሉ ህልም ኖሯል።

‹‹ህልም ቢሆንም ትልቅ ሰላም ተሰማኝ። አይኔን ዘጋሁ ‹‹ስብሃት ለእግዝአትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ!›› አልኩ። ታላቅ እፎይታ ተሰማኝ። ደስ አለኝ። አይኔን ከፈትኩ። ወለሉ ላይ ተንበርክኬአለሁ። መቼ ከአልጋ ወጣሁ? ወይስ ጪርሶ አልጋ ውስጥ አልገባሁም ነበር? በጭራሽ ላውቅ

http://ethioliberty.wordpress.com/

አልቻልኩም። አሁንም ቢሆን አላውቅም። አየህ፣ የኔ ዓለም ድንበሮቹ ተቃውሰዋል፣ የህልምንና የውንን ሀገሮች ይለይ የነበረው አጥር ፈርሶ፣ የእብደትን ውሃ ከጤንነት ሀገር ያግድ የነበረው ግድብ ፈርሶ፣ አሁን ህልምና እውን፣ እብደትና ጤንነት ድብልቅልቃቸው ወጥቷል። ኑሮዬም በጣም ግራ የገባው ውሉ የማይታወቅ፣ ውስብስብ ያለ ክር ሆኖአል››

ይህን ሁሉ ሲነግረኝ ረጋ ባለ ድምጽ ነው። ከእብደቱ ድኖ ይሆን? ወይስ እብደቱ ስለባሰበት ይሆን እንደዚህ በእርጋታ ለመናገር የሚችለው? ፈራሁ

ዝም ብሎ ጥቂት ከቆየ በኋላ ‹‹ግን አስታጥቄ አብደሃል ሲለኝ፣ ነገሩን ከእሱ አፍ ስሰማው ደነገጥኩ እንጂ፣ ማበዴንስ በፊት ነው ያወቅኩት››

‹‹ምን ትዘባርቃለህ!? ይሄ ያንተና የአስታጥቄ ዕውቀት ነው። የኔ ከአናንተ አውቀት አያንስም። ያሲን ደግሞ በአውቀት ሶስታችንንም ይጠቀልላል። እና እኔና ያሲን ስለአንተ ተነጋግረናል። ተስማምተንበታል። አብደት አይደለም››

‹‹ምንድነው ታዲያ?››

‹‹Nervous breakdown የሚሉት ነው።››

ላቅ አለ። ፈገግታው ከአብደት ንፁህ ነበር። ኋፊ ጥበብና ጥልቅ ሀዘን የሞላው ፈገግታ ነበር። ወይስ ፍፁም አብደት የተሞላው ፈገግታ ይሆን?

‹‹አይ! አንተ ጥሩ ሰው ነህ። ደግ ሰው ነህ። አስተዋይ ነህ። ግን ስለኔ የማታውቀው አንድ ነገር አለ›› አለኝ።

‹‹ምን?››

‹‹ገና አብደቱ ሳይጀምረኝ አንደሚመጣ አውቅ ነበር።›› ዝም ብዬ ሳየው አሁንም ያ ያዘነ ፈገግታው ብቅ እያለ ‹‹ይሄ አብደት አንደሚመጣብኝ ገና በልጅነቴ አውቅ ነበረ›› አለኝ

‹‹እንዴት ልታውቅ ቻልክ?››

‹‹እጣዬ ነው››

‹‹የምን እጣ ነው አሱ?››

‹‹የልደት እጣ። ከመወለድህ በፊት እጣ ይደርስሃል። አንዳንዱ የዘውድ እጣ ያደርስዋል፣ ከንጉሳዊ ቤተሰብ ያወሰዳል። እኔ የእብደት እጣ ደረሰኝ፣ ከአብድ ቤተሰብ ተወለድኩ››

‹‹አልገባኝም››

‹‹አያቴ አብደው ነው የሞቱት። የአባቴ ታላቅ ወንድም አብዶው ሞቱ። ታናሽ አህቴ ከአራት ዓመት በፊት አበደች። አገር ቤት ነው ያለችው። እና አሁን የኔ ተራ ነው።›› እጁን ሸሚዙ ስር ሰደደና ከደረቱ ስር ወርቅ ሰንሰለት ላይ የተንጠለጠለ አንድ ትንሽ የወርቅ መስቀል አወጣ። ከመስቀሉ ጋር አንድ ሌላ ነገር ተንጠልጥሏል። የተጠቀለለ ቁራጭ ቆዳ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ይህ ምን ይመስልሃል?›› አለኝ

‹‹ክታብ››

‹‹አውቀሃል። ከአብደት የሚከላከል ክታብ። እናቴ ነበረች አስደግማ ያሰረችልኝ። ግን እንደምታየው ነው። የልደትን እጣ ክታብ አይከለክለውም››

ክታቡን መልሶ ደረቱ ውስጥ ከተተ። ዝም ብሎ ቆየ

‹‹ለምን መሰለህ ይህን ሁሉ የምነግርህ?›› አለኝ

‹‹ለምንድንነው?›› አልኩት

‹‹በጣም ስለማከብርህ ነው። እንደሌሎቹ የሀገሬ ልጆች አይደለህም። እዚህ የመጣኸው ዲግሪ ፍለጋ ብቻ ሳይሆን፣ ስለሰው ፍጥረትና ባህሪይ ማወቅ እንደምትፈልግ በግልጽ ይታየኛል። ስለዚህ እውቀትህ ላይ ትንሽ ሊጨምርልህ የሚችል አንድ ነገር አለ በኔ ላይ የደረሰ። የሰውን ልጆች ጥሩነት የሚገልጽ ነው።››

‹‹ንገረኝ››

‹‹እነግርሃለሁ፣ ግን ሌሎች ጥቃቅን ነገሮች አሉ፣ ሳልረሳቸው ልነግርህ የምፈልገው። አየህ፣ አእምሮዬን እጅግም አላምነውም። ጨርሶ እስኪከዳኝ አምስት ሰዓት ያህል እንኳ አያገለግለኝም። ስለዚህ በመጀመሪያ ላመስግንህ። እንደ ደንቡ ቢሆን መጨረሻ

ላይ ነበር የማመሰግንህ። ግን በኋላ ማመስገኑን እረሳው ይሆናል።››

‹‹የምን ምስጋና ነው እሱ?››

‹‹እንደዚህ እያስቸገርኩህ ስለቻልከኝ። ሌሎቹ ሀበሾች እዚህ ይመጡና እንዳሮጊት ‹‹ጵፅ!›› ብለውኝ ይሄዳሉ። በነሱ ቤት ሀዘን መግለጻቸው ነው። ግን ምንም ባብድ የሀገሬን ልጆች አውቃቸዋለሁ። ለኔ ሲሉ አስር ደቂቃ እንኳን አልተቸገሩልኝም። አስታጥቂ እዚህ መጥቶ ቤቴን ጠረገልኝ። ልብሶቼን አጠበልኝ፣ ግን ይህን ያደረገው እኔን ለማገዝ ሳይሆን ከኔ በላይ መሆኑን ለማሳየት ነው። እኔ ተበላሽቼ እግር ሹራቦቼን እንኳ ማጠብ ሲያቅተኝ እሱ ይህን አደረገልኝ፣ ገባህ?››

‹‹ገባኝ››

‹‹ደግሞ በማበዴ ሀበሾች በጣም ነው ያፈሩብኝ፣ በጣም ነው የናቁኝ፣ አንተ ባትኖር የሚያሳፍር ነገር ይመስለኝ ነበር። በአብደት ላይ እፍረት። ይታይሃል? አንተና ያሲን ብቻ ናችሁ ሁኔታዬን አይታችሁ በእውነት ያዘናችሁልኝ። በእናንተ ዓይን የኔ እብደት አስጨናቂ ሸክም ነው እንጂ አሳፋሪ ውድቀት አይደለም። ይህ አስተያየታችሁ ብዙ አግዞኛል። ብዙ›› ዝም አለ

‹‹እኔ ምልህ፣ ከወንድ ጋር ስለመተኛት ምን አስተያየት አለህ?›› አለኝ

http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹Homosexuality ማለትህ ነው?››

‹‹አምን››

‹‹ሁለቱም ወንዶች ተስማምተው ነደረጉት እስማማበታለሁ። እኔ አድርጌው አላውቅም። ግን የሚያደርጉ ሰዎች እንደሚነግሩኝ ከሆነ ከተራው ግብረስጋ ይበልጥ ደስ ይላል።››

‹‹ነውር ወይም ሃጢአት አይመስልህም?››

‹‹በፍራሽ››

ሲያስብ ትንሽ ቆየና

‹‹ትላንት ከሰዓት በኋላ እዚህ ማን መጣ መሰለህ?›› አለኝ

‹‹ማን?››

‹‹አይሪን። ስታጫውተኝ ቆየችና ‹‹ታስታውሳለህ? አንድ ቀን Let us go to my chamber ብለሽኝ ነበር›› አለችኝ። ‹‹አስታውሳለሁ፣ እምቢ አልሽ» አልኳት።

‹‹ያን ጊዜ አላለኝኝም ነበር። አሁን ግን አለኝቶኖል›› አለችኝ

‹‹አላመንኳትም። ያን ጊዜስ ስለምናት ለምን እምቢ አለችኝ? አሁንስ ሳልጠይቃት ለምን መጣች? ግራ ገባኝ››

‹‹ምንድነው ያለኝሽ?›› አልኳት

‹‹Don't be difficult›› አለችኝ

‹‹ያገርምሃል። አንጎሉ በጣም ይከማል። አስቦ ተጣጥሮ የትም ለመድረስ አይችልም። ታዲያ አይሪን ለምን እንደመጣች ድንገት ተገለጠልኝ። እርግጠኛ ነኝ አንጎሉ አስቦት ደርሰበት አይደለም፣ ዝም ብሎ በቀጥታ ነው እውቀቱ የመጣልኝ። ምናልባት እሷ ሳታውቅ ልቧን ከፍታልኝ እኔ ደግሞ ሳይታወቀኝ ልቧ ውስጥ ተመልክቼ ይሆን? Telepathy የሚሉት ነገር ይሆን?››

ራሱን ይዞ አይኖቹን ጨፈነ። ጥቂት ቆየና ራሱን እየነቀነቀ «ያገርምሃል ልጅ» አለኝ Das Capital በጣም ከባድ መፅሐፍ ነው። እያንዳንዷ አረፍተ ነገር ከአንጎልህ ብዙ ስራ ትጠይቃለች። Das Capital ን ሶስት ሰዓት ሙሉ ያለማቋረጥ ሰማንበብ የምችልበት ጊዜ ነበር። አሁን ታዲያ አንድ ሁለት ሀሳብ ላንተ ሰላቀበልክ አንጎሉ ድክም አለው»

‹‹ታዲያ አረፋ፣ ቀስ ብለህ ትነግረኛለህ››

‹‹በኋላ ጊዜ አይኖርም፣ አሁን ብነግርህ ይሻለኛል። ከአንግዲህ እኔና አንተ ሀሳብ ለሀሳብ መወያየት የምንችል አይመስለኝም»

ልቤ ፈራ፣ ከቃላቱ የባሰ የድምፁ እርጋታ አስፈራኝ

‹‹ለምን?›› አልኩት

http://ethioliberty.wordpress.com/

«በኋላ እነግርሃለሁ። አሁን የአይሪንን ልቀጥልልህ። እስከዛው ሻይውን ጥጂ እመጣለሁ። እና ይኸውልህ፣ አይሪን ለምን እንደመጣች ታወቀኝ

‹‹ያሲን ነው የላከሽ?›› አልኳት

‹‹አይደለም። እኔው ራሴ ነኝ የመጣሁት። እንዲያውም ያሲን ለምን እዚህ እንደመጣሁ ቢያውቅ ይገለኛል» አለችኝ። እኔ ግን እሱ እንደላክት እርግጠኛ ነበርኩ። «ሁለታችሁንም በጣም አመሰግናችኋለሁ። ግን ስጦታውን ለመቀበል አልችልም›› አልኳት

‹‹አልጋ ውስጥ በጣም ጥሩ ነኝ ኮ›› አለችኝ

‹‹አማረችኝ። በጣም አማረችኝ። ግን ስጦታዋን ላለመቀበል ቆረጥኩ።››

‹‹ለምን?›› አልኩት።

የደከመ ያዘነ ፈገግታውን እያሳየኝ፣ ‹‹እርግጠኛ አይደለሁም። ግን የኩራት ኩራት ይመስለኛል። እኔ ለምኜአት እምቢ ያለችኝ ሴት ባሏ ሃጂ ስጪው ብሏት መጥታ ስትሰጠኝ ልቀበል አልፈለኩም። ግን ደግነታቸው ልቤን ነካው። በጣም አመሰገንኳት። ስታሳዝኑኝ ቆይታ ሄደች።››

ከለጭር ዝምታ በኋላ፣ ‹‹ይመስለኛል፣ ይኼ ያሲን እንደኔና እንዳንተ ተራ ሰው አይደለም›› አለኝ

‹‹አይደለም›› አልኩት

‹‹የአውቀቱን ስፋትና ጥልቀት ማለቴ አይደለም››አለኝ

‹‹አውቃለሁ›› አልኩት

‹‹ምን ታውቃለህ?››

‹‹ልቡ ንፁህ ነው››

‹‹ኧረ ከሱ ሌላ?››

‹‹ከሌቶችም ከወንዶችም ጋር ይተኛል››

‹‹ይኸን ድሮም ታውቅ ነበር?››

‹‹አዎን››

‹‹ታዲያ ልጁ አይቀፍህም?››

‹‹በጭራሽ!››

‹‹አትንቀውም?››

‹‹ቢቻለኝ ኖሮ እኔም እንደሱ መሆን በፈለኩ››

‹‹ይገርማል። በጣም በጣም broad minded ነህ›› አለኝ

ዝም ብለን ቆየን ‹‹ሻይ ደርሶ ይሆን?›› አለኝ

ሻዩን ቀድቼ ስሰጠው

‹‹ይገርማል። በልቤ ከሁሉ ሰው የማከብረው አንተን ነው። የመጨረሻ ኩባያ ሻዩን አፍልተህ የምትሰጠኝ አንተ ነህ። ጥሩ አይደለም?›› አለኝ

‹‹ምን ማለትህ ነው የመጨረሻ ኩባያ ስትል?›› አልኩት፣ ልቤን ፍርሃት እየጨበጠው

http://ethioliberty.wordpress.com/

ፊንግ አለ ‹‹ ከእንግዲህ ሻይ ልተው ነው›› አለኝ

‹‹ለምን?›› አልኩት

‹‹በኋላ እነግርሃለሁ።›› ሻዩን ከጠጣ በኋላ፣

‹‹ትላንት በስንት ሰዓት ነው ደህና እደር ብለኸኝ የሄድከው?›› አለኝ።

የእጅ ሰዓቱ ቀጭቀጭ እያለች እያስፈራራችው አውልቆ ጠረጴዛ ኪስ ከቶ ረስታት ነበር። ጊዜ በሰዓት መከፈሉንም ረስቶት ነበር ይመስላኛል። ዛሬ ግን አንድ ነገር ያደረገው በስንት ሰዓት እንደነበረ ለማወቅ ፈለገ። መዳኑ ይሆን?

‹‹አራት ተኩል ይሆናል›› አልኩት።

‹‹እንግዲያው ያሲን ወደ አምስት ሰዓት ላይ ነበር የመጣው ማለት ነው››

‹‹እኔ ከሄድኩ በኋላ?››

‹‹አዎን››

‹‹ምን ሊያደርግ መጣ?››

ፊቱ ተለወጠ። እንግዲህ ከታመመ ጀምሮ ፊቱ ላይ ከፍርሃት፣ ከሃዘንና ከድካም በቀር ሌላ ነገር አይቼ አላውቅም። ስለዚህ አሁን ፊቱ ላይ ብቅ ያለው ነገር በጣም አዲስ መስለኝ። ለጊዜው ምን እንደሆነ ለማወቅ አልቻልኩም

‹‹እንደኮ ልንገርህ? መንገሩ ያሳፍራል›› አለኝ። ፍርሃት!

‹‹ምኑ ነው የሚያሳፍረው?›› አልኩት

‹‹ድርጊቱ አያሳፍርም፣ መንገሩ ነው የሚያሳፍረው››

‹‹ታዲያ እንደኮ ይሻላል?›› አልኩት

‹‹እንዲያው በደፈናው ልንገርህ መሰለኝ››

‹‹እሺ።››

‹‹አየህ . . . ›› መቀጠል አቃተው ‹‹አየህ እንዲህ ነው፣ ይኸውልህ ታዲያ፣ ቅድም እንዳልኩህ›› ሲል ሲያምጥ ብዙ ጊዜ ቆየ። በመጨረሻ ‹‹አየህ›› አለኝ ‹‹ያሲን መጥቶ ሲያጫውተኝ አመሸ። መሸ ጊዜው፣ ገባህ ምልህ? እና ይኸውልህ ጊዜው መሸ። ሊመሽ ሆነ። በጣም መሸ ጊዜው። ገባህ ምልህ? እንግዲህ ጊዜው አልመሸም? ሲመሽ ጊዜ ያሲን ‹‹ደክሞኛል፣ በእግሬ ከምሄድ እዚህ አድሬ ባጫውትህ ምናለ?›› አለኝ። የአያሬን ሃሳብ ታየኝ ብየህ የለ? አሁንም ያሲን ለምን እንዲህ እንዳለ ወለል ብሎ ታየኝ። ለምን ታወቀኝ ይሆን? ምናልባት በሽታዬ እንደ ልዩ አይን ይሰራ ይሆን? የሆነ ሆኖ ‹‹እደር›› አልኩት

http://ethioliberty.wordpress.com/

የአየለ ፊት የባሰውን አፈረ፣ የድምፁን ስላም እፍረት አደፈረሰው። ከዚህ በኋላ የአየለ እፍረት ጠፍቶ ድምፁ ሠላማዊ ሆነ፣ ቀጠለልኝ።

‹‹እንግዲህ የሚያሳፍር ቦታ ደረስክ። እንደሌሎቹ የአገሬ ልጆች ብትሆን ይሄንን ነገር አልነግርህም ነበር። አየህ ያሲን መብራቱን አጠፋና አልጋዬ ውስጥ ገባ። እንዴት ልበልህ? በቃ . . . ሆነ ነገሩ››

‹‹ለምን እንዲህ ልታገለግለኝ ፈለግክ?›› አልኩት በጨለማው

‹‹ለራሴው ደስታ። በጣም ደስ ይለኛል›› አለኝ

‹‹አሱን ተወው! ይልቅ እውነቱን ንገረኝ›› አልኩት

‹‹ያንተ ህይወት ለኔ ምን ያህል ክፍ ያለ ዋጋ እንዳለው እንድታውቅ ብዬ ነው። አንተ ለኔ ምን ያህል ልዩነት እንደምታመጣ ልነግርህ ፈልጌ ነው። ሌላ የመንገሪያ ዘዴ አጣሁ›› አለኝ

‹‹ለምን ልትነግረኝ ፈለግህ?›› አልኩት

‹‹ብቸኝነት እንዴት ያለ ከባድ ሸክም እንደሆነ ስለማውቅ›› አለኝ

‹‹ስለብቸኝነት ምን ታውቃለህ?›› አልኩት

‹‹ብዙ ብዙ አውቃለሁ። እኔም ራሴ ብቸኛ ነኝ። እጣችን ተመሳሳይ ነው›› አለኝ

‹‹አሁን ግን እኔ ብቸኝነት አይሰማኝም›› አልኩት። ውሸቱን ነበር።

‹‹ትንሽ ቆይቶ ተነስቶ ደህና አደር ብሎኝ ሄደ። እይደንትህም የሰው ነገር? አስቲ አሁን ለምን ይህን ሊነግረኝ ፈለገ? ምነ ነኝ? ምን አድርጌለት አውቃለሁ? ... ልነግረው አልፈለክም። መከራው ሁሉ ከንቱ መሆኑን ልነግረው አልፈለክም

‹‹ከሄደ በኋላ የያዘኝን ፍርሐት እንዴት ልግለጽልህ? ክፉ ጨካኝ ፍርሃት ነበር። እንግዲህ እኔ የለመድኩት ፍርሃት ድምፆች ሆሞ ጆርናሊስት ራሲስት እያሉ ሲሰድቡኝ ሲዶልቱብኝ ነው። አሁን ግን እንዳች ድምጽ የለም። ፍፁም ፀጥታ ነው፣ በጠራራ ፀሐይ የወንዝ ዳር ፀጥታ፣ ካሁን አሁን መእት፣ መቅሰፍት፣ እርግማን እንደነጎድጓድ ሊወርዱበት የሚችል ፀጥታ፣ የሚያስፈራ ፀጥታ ተዘረጋ። እንዴት ፍርሃቱ አልገደለኝም? አሁን ይገርመኛል። ፀጥታውን እንዳልነቀንቀውና ነጎድጓድ እንዲያወርድ ፈርቼ በጀርባዬ እንደተጋደምኩ ላልንቀሳቀስ ከዓመት

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሚረዝም ጊዜ ቆየሁ። ደግነቱ ሰውነቱ ደክሞአል። ተኛሁ ፀጥታው መሐል። እንቅልፍ እንደዚህ ጥሩ ነገር የሆነ፣ ሞት እንዴት ይሆን?››

አብድ ሰው ስለአብደት ይህን ያህል ያውቃል? በእንዲህ ያለ እርጋታ ስለ አብደት ያወራል? ወይስ አየለ ድኗል? ወይስ ምንድን ነው?

ዝም ብለን ቆየን ‹‹ላስበው የኔ በሽታ ከሞት ሀገር የተላከልኝ ጥሪ መስሎ ይሰማኛል›› አለ

‹‹እንዴት?›› አልኩት

‹‹በሽታው ሲያዘኝ ፍርሃት ያንቀጠቀጠኛል። በሽታው ለጊዜው ሲሰቀኝ ደግሞ ድክም ድቅቅ ያደርገኛል። ስለዚህ ሁሉቱንም ጊዜ መሞት እመኛለሁ። ከፍርሃቱ ከመርበትበቱ ከመንቀጥቀጡ ለማምለጥ ራሴን ብገድል እወዳለሁ። ከድካሙ ለመገላገል ደግሞ እንዴ ብተኛና ተኝቼ ብቀር፣ እስከ መቼም ባልነቃ በጣም ደስ ይለኛል። ስለዚህ በፍርሃትም ሆነ በድካም ሁል ጊዜ ሞቴን እንደተመኘሁ ነው››

ልናገር አፌን ስከፍት እጁን አንስቶ አፌን አስያዘኝ

‹‹ምንም ብትናገረኝ ሃሳቤን ልታስለውጠኝ አትችልም›› አለኝ

የደከመ ያዘነ ፈገግታው ብቅ አለ፣ ንግግሩን ቀጠለ ‹‹ብስጭት-ጭት ብለህ ተስፋ ቆርጠህ አጥንትህ ሁሉ በድካም ድቅቅ ብሎ ይታይህ። ይኼኔ አንድ ንፁህ ክፍል ውስጥ በጣም ንፁህ ሆኖ የተነጠፈ፣ ምቹ አልጋ አጠገብህ አለ። ለመተኛት ትችላለህ፣ ያባትህ ቤት ነው፣ መተኛት ማንም አይከለክልህም። እትተኛም? ልብስህን አውልቀህ እትተኛም? ይሸውልህ ሞት እንደዚህ አልጋ ሆኖ ነው የሚታየኝ። እና መተኛት አፈልጋለሁ። ልብሴን ላውልቅ ነው።››

‹‹ምን?›› አልኩት። ድምጼ ከጉሮሮዬ አልወጣም። ከንፈሬን አንብቦ መልስ ሰጠኝ። ረጋ ባለ ሰላማዊ ድምጽ መለሰልኝ

‹‹ራሴን ልገል ነው። አይዞህ እትፍራ። አይገርምህም? አሁን ተራየን አይዞህ አልህ ጀመር። አንተ ብትሞት የሚያሳዝን መቀጪት ይሆናል። እኔ ብሞት ግን እረፍት ነው። አባክህ አትቃወመኝ፣ አታስቸግረኝ፣ ልታስጥለኝ ብትሞክር ታስቸግረኛለህ እንጂ አታስጥለኝም። አባክህ አታስቸግረኝ፣ ሰራሴ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ደክሞኛል። እንዴት እንደደከመኝ ብታይ፣ እንዴት ድክም እንዳለኝ ብታውቅ!

‹‹ከአራት አምስት ሰዓት በኋላ ለመምጣት የሚዘጋጀውን እብደት ሳስበው፣ መጥቶ ሊያፍነኝ፣ ሊያስጨንቀኝ የሚለለፈውን ፍርሃት ሳስበው ልቀበለው አልችልም። ደሞስ ለምን እቀበለዋለሁ? ማን ነው አፉን ምልቶ ተቀበል የሚለኝ? እኔ ኑሮን እምቢ አላልኩም። እብደትን ግን እምቢ አላለሁ። እምቢ! እምቢ! እምቢ!

‹‹አንተ እብደትህን ተቀበል፣ ፍርሃት መንቀጥቀጥህን አስተናግድ፣ ድካምህን ተሸክም ብለህ ትፈርድብኛለህ?

‹‹ይኸውልህ፣ ኑሮ ማለት በር መስኮት የሌለው ዝግ ድፍን የሆነ ክፍል ነው። ግን መውጫ አለው። ከወጡ በኋላ መመለስ አይቻልም እንጂ መውጫውስ አለ። እኔ በበኩሌ መመለስ አልፈልግም። ስለዚህ መውጣቴ ነው። መውጣቴ ነው።››

መናገር ዋጋ ያለው አልመሰለኝም። እንዲያውስ ምን ልነግረው እችል ኖሯል? ፍርሐት መንቀጥቀጡን መቼ ቀመስኩትና ልገስጸው እችላለሁ?

ድካሙን መቼ ተሸክምኩትና ልመክረው እችላለሁ? ዝም አልኩት

ክኪሱ ወረቀት አውጥቶ ሰጠኝ። ‹‹የናቱ ስምና አድራሻ ነው። ዕፈሀ በመኪና አደጋ ሞቶ እንድትላት አደራ፣ እሺ?›› አለኝ። ወረቀቱን በሚንቀጠቀጥ እጄ ተቀብዬ ኪሴ ከተትኩት። ከደረት ኪሱ ቦርሳ አውጥቶ ከውስጡ ገንዘብ አወጣ

‹‹አምስት መቶ ስልሳ ፍራንክ ነው። ደመወዜን ቅድም ተቀበልኩ። ለያሲን ስጥልኝ። ታዲያ የራስህ አስመስለህ ስጠው እሺ?›› ብሎ ሰጠኝ። በዝምታ ተቀበልኩት

‹‹እንግዲህ እብደት በፍርሐት ታጅቦ ሳይመጣብኝ እንድቀድመው ቶሎ ማለት አለብኝ።›› አለና ከወምበሩ ተነሳ

እኔም እየተነሳሁ ‹‹ምን ልታደርግ ነው?›› አልኩት። ፍርሐት ልቤን እንደ ድንጋይ ከብዶታል። ጉልበቱ ውሃ ሆኗል፣ በግድ ነው የቆምኩት።

ፊገግ አለ። ፊገግታው ውስጥ ያለው ሀዘን! ያለው ሰላም! ‹‹ልተኛ ነው›› አለኝ ‹‹ምንም ስታይ የለበት›ም። ገላዬን ቅድም ታጥቤአለሁ። ልብሴን አውልቄ ፒጃማየን ለብሼ አልጋ ውስጥ እገባና፣

http://ethioliberty.wordpress.com/



በዚህች ምሳጭ እዚህ መዳፌ ስር ያለችውን የደም ስር እበጥሳታለሁ። ከዚያ ቀስ ብሉ እንቅልፍ ይወስደኛል። በል ደህና ሁን ልተኛ ነው፡፡ አለና እጁን ዘረጋልኝ

ተምበርክኬ እጁን ሳምኩት። በዝግታ ስተምበረክኩበት አስነሳኝ። በሩን ከፈተልኝ። በቁልፉ ሲዘጋው ተሰማኝ።

አ.አ. የካቲት ፲፱፻፱ ዓ.ም

http://ethioliberty.wordpress.com/



ተምበርክኬ እጁን ሳምኩት::
በዝግታ ከተምበረከኩበት አስነሳኝ::
በሩን ከፈተልኝ:: በቁልፍ ሲዘጋው
ተሰማኝ::

AMH Igz
Igziabher, Sibhat Gebre
Sebatejaw Melak 2008
hutl 1
DFB
03010928532001

ዋጋው ብር:- 15.00

http://ethioliberty.wordpress.com/